# የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

Ethiopians' Citizen Democratic Union | Union Citoyenne Démocratique des Éthiopiens

www.slttunhzb.net sh1@ttomar.net


---

### ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ያቀረበው ፡—

# ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ሀገራዊ ፡ ቅያስ ።

ክለሳ ፡ 3 ፥ ኅዳር ፡ 18 ፡ ቀን ፡ 2017 ፡ ዓ.ም. ።

መስከረም ፡ 16 ፡ ቀን ፡ 2015 ፡ ዓ.ም. ፡ ጸድቆ ፥ ሚያዝያ ፡ 21 ፡ ቀን ፡ 2015 ፡ ዓ.ም. ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ለሕዝብ ፡ ቀረበ ፤ ወቅታዊውን ፡ ኹኔታ ፡ በማገናዘብ ፡ ተሻሽሎ ፥ ሦስተኛ ፡ ክለሳው ፡ ኅዳር ፡ 18 ፡ ቀን ፡ 2017 ፡ ዓ.ም. ፡ እንሆ ፡ ለሕዝብ ፡ ቀርቧል ።

---

[ ይህ ፡ ሰነድ ፥ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ለመሳው ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፡ ያቀረበውና ፥ **ኢትዮጵያ** ፥ ዛሬ ፡ ከምትገኝበት ፡ የውንብድና ፡ አገዛዝ ፡ ወጥታ ፥ ወደ ፡ **ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ ኹነትነት** ፡ (**የርትዕ ፡ መንግሥትነት**) ፡ የምትሸጋገርበትን ፡ መንገድ ፡ የሚያመለክት ፥ **ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ሀገራዊ ፡ ቅያስ** ፡ ነው ።

ይህ ፡ ሦስተኛው ፡ ክለሳ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፥ ወቅታዊውን ፡ ኹኔታ ፡ በማገናዘብ ፡ ዘምኖ ፥ ለሀገራዊ ፡ ውይይት ፡ እና ፡ ክንዋኔ ፡ ውሏል ። የማሻሻያ ፡ ሐሳቦችን ፡ ያበረከቱልንን ፡ ኹሉ ፡ ከልብ ፡ እናመሰግናላን ።

(የተሻሻሉት ፡ ክፍሎች ፡ በቀይ ፡ ቀለም ፡ ተለይተዋል ። )

ሰነዱ ፡ በመላ ፡ **ኢትዮጵያ** ፥ በእየከተማው ፡ በእየገጠሩ ፥ በእየቀበሌው ፡ በእየጭቃው ፡ እንዲደርስ ፡ እና ፡ ሕዝብ ፡ እንዲመክርበት ፡ ኹላችኹ ፡ እንድትተባበሩን ፡ በታላቅ ፡ አክብሮት ፡ ዐደራ ፡ እንላለን ። ]

## መግቢያ ።

**የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ፡ (ኢ.ሀ.ሥ.አ.)** ፥ በመሠረታዊ ፡ ሰነዱ[1] ፥ በ***አንቀጽ ፡ 2.5*** ፡ እና ፡ በ***አንቀጽ ፡ 2.6*** ፡ የተመለከተውን[2] ፡ ዐላማውን ፡ ለመፈጸም ፥ በ***አንቀጽ ፡ 6*** ፡ እና ፡ በ***አንቀጽ ፡ 7*** ፡ በተደነገገው ፡

---

1 **ተቀጥላ – 1ን** ፡ ይመለከቷል ።

2 የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ መሠረታዊ ፡ ሰነድ ፥ ***አንቀጽ ፡ 2.5*** ፡ እና ፡ ***አንቀጽ ፡ 2.6*** ፡—

*"2.5 ፤ መላው ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፥ በነጻ ፡ እና ፡ **ሥልጡንሕዝባዊ** ፡ ምርጫ ፡ ሠይሞ ፡ የሚያቋቁመው ፡ **ሀገራዊ ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ** ፡—*

*2.5.1 ፤ በተወሰነለት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፥ በሙሉ ፡ ነጻነት ፡ መክሮ ፡ እና ፡ ዘክሮ ፡ የሚያረቀውን ፡ **ዐዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት** ፡ ለሕዝብ ፡ አቅርቦ ፡ በማስጸደቅ ፥*

*2.5.2 ፤ በሕገ ፡ መንግሥቱም ፡ መሠረት ፡ ዐዲሱን ፡ **ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ ኹነት** ፡ (**የርትዕ ፡ መንግሥት**) ፡ በማቆም ፥ **የሥልጣን ፡ ተገቢነትን** ፡ በሀገሪቱ ፡ መልሶ ፡ ማስፈን ፥ የዚህ ፡ ሀገራዊ ፡ ሱታፌ ፡ አንድያ ፡ ዐላማ ፡ ይኾናል ።*

*2.6 ፤ ይህም ፡ ዐላማ ፡ እዳር ፡ እስካልደረሰ ፡ እና ፡ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ በሀገሪቱ ፡ እስካልሰፈነ ፡ ድረስ ፥ አንዳች ፡ ደጎኛም ፡ ኾነ ፡ ክፉኛ ፡ ለውጥ ፡ በሀገሪቱ ፡ ቢከታተል ፥ የሕዝብን ፡ እግዚእና ፡ ለዘለቄታው ፡ የማስከበሩ ፡ ሰላማዊው ፡ የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ትግል ፡ እስከ ፡ ሙሉ ፡ ክንዋኔው ፡ ድረስ ፡ ሳይቋረጥ ፡ ይቀጥላል ። "*

የሥራ ፡ ድቅን ፡ መሠረት ፥ **ኢትዮጵያን** ፡ ከውንብድና ፡ አገዛዝ ፡ አውጥቶ ፡ ወደ ፡ **ሥልጡንሕዝባዊ** ፡ አገዛዝ ፡ የሚመራውን ፡ ***ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ሀገራዊ ፡ ቅያስ*** ፡ እንደሚከተለው ፡ ዘርዝሮ ፡ ለመላው ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፡ እና ፡ ለሚመለከታቸው ፡ ኹሉ ፡ በታላቅ ፡ አክብሮት ፡ እንሆ ፡ ያቀርባል ።

### 0.1 ፲ የሰላማዊ ፡ መፍትሔ ፡ አስገዳጅነት ።

0.1.1 ፲ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ የሚገዳደልበት ፡ ምክንያት ፡ የሕጋዊ ፡ መንግሥት ፡ መታጣት ፡ እንጂ ፥ የውጭ ፡ ጠላት ፡ ሀገሪቱን ፡ ወሯት ፡ አይደለም ። ባኹኑ ፡ ሰዓት ፥ መሣሪያን ፡ አንሥተው ፡ የሚዋጉ ፡ ኀይሎች ፡ ኹሉ ፥ ሰላማዊውን ፡ መፍትሔ ፡ በመምረጥ ፥ ውጊያውን ፡ አቁመው ፥ እንዋጋለታለን ፡ የሚሉት ፡ ሕዝብ ፡ በሰላማዊ ፡ እና ፡ በ**ሥልጡንሕዝባዊ** ፡ መንገድ ፡ ችግሮቹን ፡ ኹሉ ፡ የሚፈታበትን ፡ የሀገራዊ ፡ ዕርቀ ፡ ሰላም ፡ እና ፡ **የሀገር ፡ ክዋኔ** ፡ ኺደትን ፡ በሀገራዊነት ፡ መንፈስ ፡ እንዲቀላቀሉት ፡ ጥሪያችንን ፡ በሀገር ፡ ፍቅር ፡ ማስሰማታችን ፡ ይታወሳል ። ነገር ፡ ግን ፡ የመንግሥትነት ፡ ጠባይም ፡ ኾነ ፡ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ ሳይኖረው ፡ ራሱን ፡ "**ኢ.ፌ.ዴ.ሪ.**" ፡ ብሎ ፡ የሰየመው ፡ ባዕድ–ተከል ፡ የውንብድና ፡ ይዘት ፥ "አስተዳድረዋለኹ" ፡ በሚለው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ከሚያዝያ ፡ 2015 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፡ የለየለት ፡ ጦርነትን ፡ ያካኼዳል ።

0.1.2 ፲ **የኢ.ፌ.ዴ.ሪ.** ፡ ባዕድ–ተከል ፡ **ይዘት** ፡ እና ፡ "ሕገ ፡ መንግሥቱ" ፥ የችግሩ ፡ ዋነኛዎቹ ፡ ምክንያቶች ፡ መኾናቸው ፡ በመላው ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፡ ስለ ፡ ታመነ ፥ ይዘቱ ፡ እና ፡ የሚመሩት ፡ ሕዋሳት ፥ ቢቻል ፡ በውዴታ ፥ አለዚያ ፡ በግዴታ ፡ ከሥልጣኑ ፡ ሰገነት ፡ ተወግደው ፥ ዐዲስ ፡ **ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት** ፡ ሊተካቸው ፡ ይገባል ።

0.1.3 ፲ **ኢ.ሀ.ሥ.አ.** ፡ የተቋቋመው ፡ ይህኑ ፡ **የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ እግዚእና** ፡ ለማስከበር ፡ እና ፡ በዐዲሱ ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ክዋኔ** ፡ (ሕገ ፡ መንግሥት) ፡ የኢትዮጵያን ፡ የርትዕ ፡ ኹነት ፡ (የርትዕ ፡ መንግሥት) ፡ ለመከወን ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ይህ ፡ የተቀደሰ ፡ ሀገራዊ ፡ ዐላማ ፡ የመላው ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፡ ዐላማ ፡ ነውና ፥ መላው ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፥ የአንድነቱን ፡ ትእምርት ፡ ቃል ፡—

ኢትዮጵያ፡ታበጽሕ፡እደዊሃ፡ኀበ፡እግዚአብሔር።

ኢ ሀ ሥ አ

በማንገብ ፥ ለሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካሉ ፡ ለ**ኢ.ሀ.ሥ.አ.** ፡ ፈጥኖ ፡ እንዲያብር ፡ እና ፡ ከትግሉ ፡ እንዲቀላቀል ፡ ጥሪውን ፡ በሀገር ፡ ፍቅር ፡ ያስተላልፍለታል ።

0.1.4 ፲ **ኢትዮጵያ** ፡ ህልውናዋን ፡ እና ፡ ሰላሟን ፡ ለማስጠበቅ ፡ በምትታገልበት ፡ በዚህ ፡ ወቅት ፥ መከፋፈልን ፣ ማበጣበጥን ፣ ማጠፋፋትን ፡ እና ፡ የመሳሰሉትን ፡ ወንጀሎች ፡ በ**ኢትዮጵያ** ፡ ውስጥ ፡ የሚያስፈጽሙ ፡ የውጭ ፡ ኀይሎች ፡ ኹሉ ፥ የዘለቁታ ፡ ጥቅማቸውን ፡ በማሰብ ፥

ከዚህ ፡ ርኩስ ፡ ግብራቸው ፡ እንዲቈጠቡ ፡ በጥብቅ ፡ እናሳስባለን ።

## 0.2 ፤ የኢትዮጵያ ፡ ቋሚ ፡ እና ፡ ጊዜያዊ ፡ ኹኔታ ።

0.2.1 ፤ **ኢትዮጵያ** ፡ ጥንታዊት ፡ **ሥልጣኔ** ፡ እና ፡ ጥንታዊት ፡ **ሀገር** ፡ ናት ፤ በራሷ ፡ ፈቃድ ፡ ትታደሳለች ፡ እንጂ ፡ በባዕዳን ፡ እብሪት ፡ ፈርሳ ፡ ዳግም ፡ አትሠራም ።

0.2.2 ፤ በ1983 ፡ ዓ.ም. ፡ ተወጥኖ ፡ የነበረው ፡ ሰላማዊ ፡ የሽግግር ፡ ወቅት ፥ **በተባበሩት ፡ የአሜሪካ ፡ ኹነቶች ፡ እና ፡ በግብር ፡ ዐበሮቻቸው** ፡ በተፈጸመ ፡ **ነውረኛ ፡ የሽምግልና ፡ ክዳት** ፡ ምክንያት ፥ ኺደቱ ፡ ጨንግፎ ፥ **ኢትዮጵያ** ፡ ለባሰ ፡ የጦርነት ፡ እና ፡ የመበ፟ታተን ፡ አደጋ ፡ ተዳርጋለች ፤ እስከ ፡ ዘመናችን ፡ ድረስ ፡ ከችግር ፡ አልወጣችም ።

0.2.3 ፤ **ኢትዮጵያን** ፡ ለማፈራረስ ፥ በእነዚህ ፡ የውጭ ፡ ኀይሎች ፡ ቀጥተኛ ፡ ድጋፍ ፡ በሕገ ፡ ወጥ ፡ መንገድ ፡ በ1987 ፡ ዓ.ም. ፡ የተቋቋመው ፡ **የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ የውንብድና ፡ ይዘት** ፥ ርሱ ፡ ራሱ ፡ ቀድሞ ፡ በሙስና ፡ የመፈራረስ ፡ አደጋ ፡ አግኝቶት ፥ በጥቅምት ፡ ወር ፡ 2013 ፡ ዓ.ም. ፡ በሕ.ወ.ሐ.ት. ፣ በኦ.ሕ.ዴ.ድ.-ኦ.ነ.ግ. ፡ እና ፡ በሻዕቢያ ፡ ሤራ ፡ በተፈጸመ ፡ **ሀገርን** ፡ የመናድ ፡ የክዳት ፡ ጥቃት ፡ ምክንያት ፥ **የኢትዮጵያ** ፡ ኹኔታ ፡ ድንገት ፡ ወደ ፡ አጠቃላይ ፡ የሰላም ፡ መደፍረስ ፡ ተለውጦ ፥ እንሆ ፡ ዛሬ ፥ አብዛኛው ፡ **የኢትዮጵያ** ፡ ክፍል ፡ በሥልጣን ፡ ጦርነት ፡ ውስጥ ፡ ተዘፍቆ ፡ ይገኛል ።

0.2.4 ፤ ሀገራዊውን ፡ እና ፡ አሀጉራዊውን ፡ ኹኔታ ፡ በማገናዘብ ፥ መላው ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፡ የሀገሩን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጥንታዊ ፡ ክዋኔ ፡ ሊያድስ ፡ እና ፡ ሊያዘምን ፡ መብቱ ፡ የኾነለትን ፡ ያኽል ፥ ወቅታዊው ፡ ኹኔታም ፡ አስገድዶታል ። ይህንም ፡ ለመፈጸም ፥ ለሕዝብ ፡ እና ፡ ለሀገር ፡ ጠንቅ ፡ የኾነውን ፡ **የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ባዕድ-ተከ፟ል ፡ የውንብድና ፡ ይዘት** ፥ ሕዝቡ ፡ ራሱ ፡ በሰላማዊ ፡ መንገድም ፡ ኾነ ፡ በትጥቅ ፡ ትግል ፡ አስቀድሞ ፡ ሊያስወግደው ፡ ይገ፟ባዋል ።

## 0.3 ፤ ወደ ፡ ዘላቂ ፡ መፍትሔ ።

0.3.1 ፤ ወደ ፡ ዘላቂው ፡ መፍትሔ ፡ ለማምራት ፥ **የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ባዕድ-ተከ፟ል ፡ የውንብድና ፡ ይዘት** ፡ ተወግዶ ፥ ኹሉም ፡ ወገኖች ፡ **የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ እግዚእና** ፡ በማክበር ፥ መላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ በሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንገድ ፡ በሚወክላቸው ፡ ባለሥልጣኖቹ ፡ አማካይነት ፡ እና ፡ በእነርሱ ፡ ብቻ ፡ ዐዲሱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክዋኔ ፡ ሊሠ፟ራ ፡ እንደሚገ፟ባው ፡ መቀበል ፡ ይኖርባቸዋል ።

0.3.2 ፤ መላው ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፥ ሀገራዊ ፡ **እግዚእናውን** ፡ በመላ ፡ **ኢትዮጵያ** ፡ በገቢር ፡ አስከብሮ ፥ ዐዲሱን ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ክዋኔ** ፡ (ወይም ፡ **ሕገ ፡ መንግሥት**) ፡ **በሥልጡንሕዝባዊ** ፡ መንገድ ፡ መከወን ፡ አንድያው ፡ የትግሉ ፡ ዐላማ ፡ መኾኑን ፡ ያውቀዋል ። ዐላማውንም ፡ እዳር ፡ ለማድረስ ፥ ለሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካሉ ፡ **ለኢ.ሀ.ሥ.አ.** ፡ በማበር ፡ ትግሉን ፡ ሊያረ፟ጋምደው ፡ እና ፡ ኺደቱን ፡ ሊያቀለጥፈው ፡ ይችላል ።

0.3.3 ፤ **በምልክዮሽ** ፡ (በ"**ኢምፔሪያሊዝም**") ፡ ኀይሎች ፡ ሤራ ፥ በ1985 ፡ ዓ.ም. ፡ ከ**ኢትዮጵያ** ፡ በጉልበት ፡ እና ፡ በሸር ፡ እንዲገነጠል ፡ የተደረገው ፡ 14ኛው ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ክፍለ ፡ ሀገር** ፡ ኤርትራ ፡ (የባሕር ፡ ምድር ፡ እና ፡ የደንከል ፡ ጥንታውያን ፡ **የኢትዮጵያ** ፡ ግዛቶች) ፥ ተመልሶ ፡ በ**ኢትዮጵያ** ፡ ሕጋዊ ፡ አካልነቱ ፡ እንዲገኝ ፦

- **የ"ሻዕቢያ" ፡ የውንብድና ፡ ይዘት** ፡ በሕጋዊ ፡ መንገድ ፡ ተወግዶ ፥
- የክፍለ ፡ ሀገሩ ፡ ወረዳዎች ፡ ኹሉ ፥

ሕጋውያን ፡ ተወካዮቻቸውን ፡ **በሥልጡንሕዝባዊ** ፡ *መንገድ* ፡ በመሠየም ፥ **በኢትዮጵያ** ፡ **የሀገር** ፡ **ክዋኔ** ፡ ኺደት ፡ ሙሉ ፡ ተሳታፊዎች ፡ እንዲኾኑ ፥

- በተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ (ተ.መ.ድ.) ፡ እና ፡ በአፍሪቃ ፡ ኅብረት ፡ (አ.ኅ.) ፡ በኩል ፡ ንግግር ፡ ይዠመራል ።

0.3.4 ፤ እስካኹን ፥ **በኢትዮጵያ** ፡ አንጻር ፡ የተፃራሪነት ፡ አቋም ፡ የነበራቸው ፡ የውጭ ፡ ኀይሎችም ፥ ቢችሉ ፥ አቋማቸውን ፡ በማሻሻል ፥ **ኢትዮጵያን** ፡ እንዲደግፉ ፤ አለዚያ ፡ ግን ፡ የዘለቄታ ፡ ጥቅማቸውን ፡ በማሰብ ፥ **የኢትዮጵያን ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የመሸጋገሪያ ፡ ወቅት** ፡ ከማደናቀፍ ፡ እንዲጠበቁ ፡ ዳግመኛ ፡ እናሳስባለን ።

## ምዕራፍ ፡ 1 ፤

## የኢትዮጵያ ፡ ወቅታዊ ፡ ኹኔታ ፡ ፈጣን ፡ መፍትሔን ፡ ይሻል ።

**1.1 ፤ ከ 1966 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፡ በተከታተሉ ፡ የውንብድና ፡ ይዘቶች ፥ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥታውያን ፡ ሕዋሳት ፡ እና ፡ ተቋማት ፥ ለጥፋት ፡ ዐላማ ፡ ውለዋል ።**

**1.2 ፤ ባኹኑ ፡ ሰዓት ፥ ሀገርን ፡ የማፈራረስ ፡ ተልእኮ ፡ በተግባር ፡ ይፈጸማል ፤ ይህንም ፡ ለመቃወም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በአንድነት ፡ ተነሥቷል ።**

1.2.1 ፤ የችግሩ ፡ መነሻ ፡ **ባዕድ−ሠራሹ ፡ "ሕገ ፡ መንግሥት"** ፡ እና ፡ ለምእት ፡ ዓመታት ፡ የተመራው ፡ **የምልክዮሽ ፡ የንጥቂያ ፡ ስውር ፡ ጦርነት** ፡ ነው ።

1.2.2 ፤ ይህን ፡ የባዕዳንን ፡ ደባ ፡ ለመቶ ፡ ዓመታት ፡ ሲያስታምመው ፡ የቈየው ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፥ መጨረሻውን ፡ እማይፈልገው ፡ የሥልጣን ፡ ጦርነት ፡ ውስጥ ፡ ስላገባው ፥ አኹን ፡ ላይ ፥ "በቃኝ ! " ፡ ብሎ ፥ ለመጨረሻው ፡ የሞት ፡ ሽረት ፡ ፍልሚያ ፡ ቈርጦ ፡ ተነሥቷል ።

**1.3 ፤ ሀገርን ፡ የመታደጉ ፡ አጠቃላይ ፡ ሕዝባዊ ፡ ትግል ፡ እየተጠናከረ ፡ ይቀጥላል ።**

1.3.1 ፤ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፥ ባልሞት ፡ ባይ ፡ ተጋዳይነት ፤ ባልቀማም ፡ ባይ ፡ ታጋይነት ፥ ለነጻነቱ ፡ እና ፡ ለርስቱ ፡ መታገሉን ፡ በመላ ፡ ሀገሩ ፡ አጠናክሮ ፡ ቀጥሏል ።

1.3.2 ፤ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፡ ስሜት ፥ ዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፥ አንድ ፡ ኾኗል ፤ ሀገሩ ፡ **ኢትዮጵያ** ፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ **የውንብድና ፡ ይዘት** ፡ ሀገራዊ ፡ ክዳት ፡ እንደተፈጸመባት ፡ አስረግጦ ፡ ዐውቋል ።

1.3.3 ፤ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ን ፡ መወገድ ፡ የማይመኝ ፡ የኅብረተሰብ ፡ ክፍል ፡ አይገኝም ። ኾኖም ፥ ጠቅላላውን ፡ ሕዝብ ፡ ላንድ ፡ ሀገራዊ ፡ ዐላማ ፡ አስተባብሮ ፡ የሚመራው ፡ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካሉ ፡ **ኢ.ሀ.ሥ.አ.** ፡ የትግሉን ፡ ጕራ ፡ ገና ፡ ባለመቈጣጠሩ ፡ ምክንያት ፥ ሕዝቡ ፡ በተናጠል ፡ ወይም ፡ በወገን ፡ በወገኑ ፡ ተለያይቶ ፡ እስካኹን ፡ የመራው ፡ ትግል ፡ በውጤት ፡ ረገድ ፡ መለስተኛ ፡ ኾኖበታል ።

1.3.4 ፤ ከ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፥ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፡ በፋኖ ፡ ሀገራዊ ፡ ንቅናቄው ፡ እጅግ ፡ አስተማማኝ ፡ መከላከልን ፡ በማሳየቱ ፥ ከእንግዲህ ፡ ይህን ፡ ሕዝባዊ ፡ ኀይል ፡ በመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፦

- በኢትዮጵያ ፡ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ መደበኛ ፡ የጦር ፡ ሰራዊትነት ፡ በማቋቋም ፥
- ወጥ ፡ በኾነም ፡ የእዝ ፡ ተዋረድ ፡ በማዋቀር ፥

የትግሉን ፡ ግሥጋሤ ፡ ማፍጠን ፡ ይቻላል ።

1.3.5 ፤ ይህንም ፡ በመገንዘብ ፥

« *በሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነታችን ፡ ሀገራዊ ፡*

*እግዚእናችንን ፡ እናስከብር » ፡ ለሚለው ፡ አንድያ ፡ ሀገራዊ ፡ ዐላማ ፡ ኹሉንም ፡ ሀገራውያን ፡ ኀይሎች ፡ የማዋሐዱ ፡ ተግባር ፡ እየተጠናከረ ፡ ይቀጥላል ።*

1.3.6 ፤ ያንኑ ፡ ያኽል ፥ ትግሉን ፡ ጠልፎ ፡ የማጨንገፉ ፡ ግብር ፡ ዘወትር ፡ በጠላት ፡ ሠርጎ-ገቦች ፡ በሰፊው ፡ መፈጸሙም ፡ ይታወቃል ። ጠላትም ፡ ይህን ፡ ርኩስ ፡ ግብሩን ፡ ለማሳካት ፡ **የሕዝብ ፡ ውክልና** ፡ እንዳይከናወንና ፥ ርሱ ፡ ራሱ ፡ በ"**ገጽታ ፡ ግንባታ**" ፡ ባዘጋጃቸው ፡ አሻንጉሊቶቹ ፡ አማካይነት ፡ የሕዝብን ፡ መሥዋዕትነት ፡ መና ፡ ለማስቀረት ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ይሞክራል ።

1.3.7 ፤ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እግዚእናን ፡ ረምርሞ ፥ ከሕዝብ ፡ ውክልና ፡ ውጪ ፥ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ትግል ፡ በወገን ፣ በ"ፓርቲ" ፣ በጎሳ ፣ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በተርታ ፡ ውንብድና ፡ ከፋፍሎ ፡ የሚያዳክም ፡ ማንኛውም ፡ ኀይል ፥ እንደ ፡ ኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ኀላፊዎች ፡ ኹሉ ፥ በሕግ ፡ ይጠየቃል ።**

### 1.4 ፤ የኢትዮጵያ ፡ እና ፡ ያካባቢው ፡ ሰላም ፡ ደፍርሷል ፤ ወደለየለት ፡ የሥልጣን ፡ ጦርነትም ፡ አምርቷል ።

**የኢትዮጵያ** ፡ ሰላም ፡ መታወክ ፥ ለአፍሪቃ ፡ ቀንድ ፡ ሀገሮች ፡ ስያሳዊ ፡ መዘናበል ፡ እና ፡ መናጋት ፡ ምክንያት ፡ ኾኖ ፥ በሚሊዮን ፡ የሚቈጠሩ ፡ ነዋሪዎቻቸውን ፡ ለባሰ ፡ መፈናቀል ፡ እና ፡ ስደት ፣ ረኃብ ፡ እና ፡ ሞት ፡ እንደ ፡ ዳረጋቸው ፡ ተረጋግጧል ።

### 1.5 ፤ ይህን ፡ ከፊታችን ፡ የተደቀነውን ፡ የመከራ ፡ አዙሪት ፡ ለመስበር ፥ የኢትዮጵያ ፡ ስያሳዊ ፡ ችግር ፡ መፈታት ፡ ዐይነተኛው ፡ ምክንያት ፡ ይኾናል ።

## ምዕራፍ ፡ 2 ፤

## የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ለምን ፧ በማን ፧ በምን ፧ እንዴት ፧ መቼ ፧ እስከ ፡ መቼ ፧

### 2.1 ፤ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ለምን ፧

2.1.1 ፤ **የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ የውንብድና ፡ ይዘት** ፡ የመጨረሻ ፡ ተልእኮ ፥ ወይም ፥ የተፈጠረለት ፡ የጥፋት ፡ ዐላማ ፥ **ኢትዮጵያን** ፡ መበታተን ፡ እና ፡ **ለምልክዮሽ** ፡ የብዝበዛ ፡ ዐቅድ ፡ በሚመች ፡ መንገድ ፥ ፍርስራሹን ፡ "በአፍሪቃ ፡ ቀንድ ፡ ተዳብሎ" ፡ (confederation) ፡ መልሶ ፡ ማዋቀር ፡ ነው ።

2.1.2 ፤ ጥንትም ፡ **ሀገር ፡ ኢትዮጵያን** ፡ የሠራት ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ሥልጡን ፡ ሕዝብ** ፡ በአንድነቱ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ዛሬም ፡ **ሀገር ፡ ኢትዮጵያን** ፡ ለማፈራረስ ፡ የተነሡበትን ፡ ኀይሎች ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ሥልጡን ፡ ሕዝብ** ፡ በአንድነቱ ፡ ያስወግዳቸዋል ።

2.1.3 ፤ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፡ በአንድነቱ ፥ የሀገሩን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ነጻነት ፡ እና ፡ አንድነት ፣ ልማት ፡ እና ፡ እድገት ፡ ከመመኘት ፡ በቀር ፥ መፈራረሷን ፡ አይመኝም ፤ የምልክዮሽንም ፡ የብዝበዛ ፡ ዐቅድ ፡ ይቃወማል ።

2.1.4 ፤ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፡ በሀገሩ ፡ በኢትዮጵያ ፥ እግዚእናው ፣ ሰላሙና ፡ ነጻነቱ ፡ ተከብረውለት ፡ የመኖር ፡ የተቀደሰ ፡ መብቱ ፡ ሊገሰስ ፡ አይገባም ።

### 2.2 ፤ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ በማን ፧

2.2.1 ፤ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፡ የኢትዮጵያ ፡ አንድያ ፡ ባለቤት ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፥ በሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካሉ ፡ **ኢ.ሀ.ሥ.አ.** ፡ አማካይነት ፥ እግዚእናውን ፡ በመላ ፡ ሀገሩ ፡ ላይ ፡ ሊያስከብርና ፥ ራሱን ፡ በራሱ ፡ የሚገዛበትን ፡ ኹነቱን ፡ (ወይም ፡ መንግሥቱን) ፡ መልሶ ፡ ሊከውን ፡ ይገደዳል ። ይህም ፥ በቅድሚያ ፡ **ኢትዮጵያን** ፡ በዐዲስ ፡ **ክዋኔ** ፡ ወይም ፡ በዐዲስ ፡ **ሕገ ፡ መንግሥት** ፡ መከወንን ፡ ይጠይቃል ።

2.2.2 ፤ በማንኛውም ፡ የመንግሥታዊ ፡ ሥልጣን ፡ ዕርከን ፡ በባለሥልጣንነት ፡

የሚሾሙትም ፡ ኾኑ ፡ በተርታ ፡ ሠራተኛነት ፡ የሚቀጠሩት ፥ **ኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራውያን** ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

2.2.3 ፤ ኢትዮጵያውያን ፡ የስያሳ ፡ ቡድኖች ፡ ወይም ፡ "የፖለቲካ ፡ ፓርቲዎች" ፥ **የሕዝብ** ፡ እና ፡ **የሀገር** ፡ አገልጋዮች ፡ እንጂ ፥ **የሀገር** ፡ ባለቤቶች ፡ ስላልኾኑ ፥ ይህ ፡ ዐዲስ ፡ ሀገራዊ ፡ **ክዋኔ** ፡ እስከሚከወን ፡ ድረስ ፥ በሀገራውያን ፡ አባላታቸው ፡ አማካይነት ፥ በነፍስ-ወከፍ ፡ ደረጃ ፡ ከ**ሀገር ፡ ክዋኔ** ፡ ኺደቱ ፡ ሊሳተፉ ፡ ባለሙሉ ፡ መብት ፡ ናቸው ።

2.2.4 ፤ **ሥሉጣን ፡ ማኅበሮች** ፡ ("civic" ፡ ማኅበሮች) ፥ ለርትዕ ፡ ተሚጋኞች ፡ እና ፡ **የሥልጣኔ** ፡ ሰባኪዎች ፡ እንደ ፡ መኾናቸው ፡ መጠን ፥ ይህን ፡ **ሥልጡንሕዝባዊ** ፡ ሀገራዊ ፡ **የክዋኔ** ፡ ኺደት ፡ ሊደግፉ ፡ እና ፡ ሊያመቻቹ ፡ ይገባል ፤ ሱታፌያቸውም ፡ ይፈለጋል ።

2.2.5 ፤ **ኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራውያን** ፡ እና ፡ ባዕዳን ፡ ባለሚያዎች ፥ በማማከር ፡ ደረጃ ፡ የሚሳተፉበት ፡ አገባብ ፡ ይኖራል ፤ ዝርዝሩ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይገለጻል ።

2.2.6 ፤ ጎረቤቶች ፡ ሀገሮች ፡ ከ**ኢትዮጵያ** ፡ ጋራ ፥ ጥንት ፥ ባንድ ፡ መንግሥትነት ፡ ተዋሕደው ፡ የነበሩትን ፡ ያኽል ፥ ወደ ፡ ፊት ፡ ደግሞ ፡ ባንዲት ፡ **ሥልጡንሕዝባዊት ፡ ሀገር ፡ ኢትዮጵያ** ፡ ተዋሕደው ፡ የሚኖሩበት ፡ ዕድል ፡ ዛሬ ፡ ተፈጥሯል ፤ አህጉራዊው ፡ አዝማሚያም ፡ ይህኑ ፡ የሚያበራታ ፡ ኾኗል ። ውዴታቸው ፡ የሚኾንላቸው ፡ ጎረቤቶች ፡ ሀገሮች ፡ ኹሉ ፥ ይህን ፡ የመዋሐዱን ፡ የመዠመሪያ ፡ ርምጃቸውን ፡ የሚፈጽሙበትን ፡ የሱታፌ ፡ ዕድል ፡ በዚህ ፡ **የሀገር** ፡ **ክዋኔ** ፡ ኺደት ፡ ያገኛሉ ። ከተመልካችነት ፡ እስከ ፡ ፍጹም ፡ ተሳታፊነት ፡ በሚዘረጋ ፡ አገባብ ፡ በኺደቱ ፡ ሊረማመዱ ፡ ይችላሉ ።

2.2.7 ፤ **የዓለም ፡ መንግሥታት** ፡ በ**ኢትዮጵያ** ፡ ሰላም ፡ እና ፡ ልማት ፡ ቀጥተኞች ፡ ተጠቃሚዎች ፡ ስለሚኾኑ ፥ **የኢትዮጵያን** ፡ **እግዚእና** ፡ በማክበር ፥ **ሥልጡንሕዝባዊ** ፡ ኺደቱን ፡ ሊከታተሉም ፥ አስፈላጊ ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፥ ድጋፉቸውን ፡ ሊያበረክቱለት ፡ ይችላሉ ።

2.2.8 ፤ **የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅትን** ፡ እና ፡ **የአፍሪቃ ፡ ኅብረትን** ፡ ጨምሮ ፥ **አህጉራውያን ፡ ድርጅቶች** ፣ **ተቋሞች** ፡ እና ፡ **የልማት ፡ አጋሮች** ፡ ኹሉ ፥ ይህን ፡ **ሥልጡንሕዝባዊ** ፡ የሀገር ፡ **ክዋኔ** ፡ ኺደት ፡ ሲደግፉ ፥ አህጉራውያን ፡ ግቦቻቸውን ፡ ማሳካትም ፡ መኾኑን ፡ ዐውቀው ፥ ሙሉ ፡ ትብብራቸውን ፡ ሊቸሩት ፡ ይገባል ።

## 2.3 ፤ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ በምን ፦

2.3.1 ፤ **የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት** ፡ የሚቋቋመው ፡ በሥልጡንሕዝባዊ ፡ **የሕዝብ ፡ ውክልና** ፡ መሠረት ፡ ብቻ ፡ ይኾናል ።

2.3.2 ፤ ይህም ፥ **ከቀበሌ** ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ወረዳ ፣ አውራጃ ፣ **ክፍለ ፡ ሀገር** ፡ እና ፡ እስከ ፡ መላ ፡ **ኢትዮጵያ** ፥ በእየዕርከኑ ፡ ተከታትሎ ፡ በሚያርግ ፡ **ሥልጡንሕዝባዊ** ፡ የውክልና ፡ ሥርዐት ፡ መሠረት ፡ ይኾናል ።

2.3.3 ፤ **የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥቱም** ፡ በ**ሥልጡንሕዝባዊ**ው ፡ የውክልና ፡ ሥርዐት ፡ መሠረት ፡ በመላ ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፡ የተወከሉት ፡ እንደራሴዎች ፡ በጉባኤ ፡ የሚሠይሙት ፡ ጊዜያዊ ፡ እና ፡ **ሀገራዊ ፡ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት** ፡ ይኾናል ።

2.3.4 ፤ **የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥቱ** ፡ የውከላ ፡ ስያሳዊ ፡ መሠረት ፡ በኢ.ህ.ሥ.አ. ፡ "**መሠረታዊ ፡ ሰነድ**" [3] ፡ ላይ ፡ በሰብሳቢ ፡ አነጋገር ፡ ተመልክቷል ፤ የውከላው ፡ አፈጻጸም ፡ እና ፡ አወቃቀር ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይፋ ፡ በሚወጣ ፡ "**መዋቅራዊ ፡ ሰነድ**" ፡ አማካይነት ፡

3 ተቀጥላ - 1ን ፡ ይመለከቷል ።

በዝርዝር ፡ ይገለጻል ።

2.3.5 ፤ በግስ ፡ ረገድ ፡ አለመግባባት ፡ እንዳይኖር ፥ ሙሉ ፡ ስምምነትም ፡ እንዲገኝ ፥ **ዐጪር ፡ የስያሳ ፡ ቃላት ፡ መፍቻ ፡ በተቀጥላ – 2** ፡ ታክሏል ። አህጉራውያን ፡ ንጽጽሮችን ፡ ለመፈጸም ፡ እንዲያመች ፥ የእንግሊዝኛ ፡ ትርጉሞችም ፡ ታክለውለታል ። ከዚህ ፡ ጋራ ፥ ዐውደ ፡ ቀለም [4] ፡ የተባለው ፡ ነጻ ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፡ መግበር ፥ በፊደል ፡ ጥንቀቃም ፡ ኾነ ፡ በትርጉም ፡ ጥንቀቃ ፡ ረገድ ፡ የተሟላ ፡ አገልግሎትን ፡ ስለሚሰጥ ፥ **የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት** ፡ የእየዕርከኑ ፡ ሥልጣኖች ፡ እና ፡ የእየዘርፉ ፡ ድርጅቶች ፥ ዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፥ በመደበኛነት ፡ እንዲሠሩበት ፡ ይደረጋል ።

2.3.6 ፤ **የሀገራዊው ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ ፡ አባላት ፡ የውከላ ፡ ኺደት** ፡ **በተቀጥላ – 3** ፡ በሥዕላዊ ፡ መልክ ፡ ተመልክቷል ።

2.3.7 ፤ **የኢትዮጵያ ፡ ክፍላተ ፡ ሀገር** ፣ በነዋሪዎቻቸው ፡ ብዛት ፡ አንጻር ፡ የሚኖሯቸው ፡ **የተወካዮች ፡ ብዛት** ፡ **በተቀጥላ – 4** ፡ ላይ ፡ በጊዜያዊነት ፡ ተዘርዝሯል ።

## 2.4 ፤ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ እንዴት ፥

2.4.1 ፤ **የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ የውንብድና ፡ ይዘት** ፡ **የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥትን** ፡ ጉዳይ ፡ የሚቀበልበት ፡ ወይ ፡ የሚገፋበት ፡ መንገድ ፡ **የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥትን** ፡ የክንዋኔ ፡ ስልት ፡ እና ፡ ኺደት ፡ ይወስናቸዋል ።

2.4.2 ፤ **የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ የውንብድና ፡ ይዘት** ፥ ከሚያዝያ ፡ ወር ፡ 2015 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ የርምረማ ፡ ዘመቻን ፡ በግልጽ ፡ በመገፍመሩ ፥ ከሐምሌ ፡ ወር ፡ 2015 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፡ ደግሞ ፡ የርምረማ ፡ ዘመቻውን ፡ ወደለየለት ፡ ጦርነት ፡ በማባባስ ፥ መላውን ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፡ በጦር ፡ ሰራዊት ፡ ኀይል ፡ በመጨፍጨፉ ፥ ሰላማዊ ፡ መፍትሔን ፡ ገፍቷል ፥ ራሱንም ፡ ከመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ምሥረታ ፡ ኺደት ፡ ወግዷል ። በዚህ ፡ አድራጎቱ ፥ **የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ የውንብድና ፡ ይዘት** ፡ በኢትዮጵያ ፡ አንጻር ፡ በጠላትነት ፡ መሰለፉን ፡ አረጋግጧል ።

2.4.3 ፤ **የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ የውንብድና ፡ ይዘት** ፡ **የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥትን** ፡ ሐሳብ ፡ ገፍቶ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ጠላትነት ፡ ስለተሰለፈበት ፥ መላ ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፡ ሊነሣበት ፡ እና ፡ በኀይል ፡ ሊያስወግደው ፡ ተገዷል ። በዚህም ፡ መሠረት ፥ **ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ የውንብድና ፡ ይዘት** ፡ ራሳቸውን ፡ ነጻ ፡ የሚያወጡ ፡ ቀበሌዎች ፣ ወረዳዎች ፣ አውራጃዎች ፡ እና ፡ ክፍላተ ፡ ሀገር ፥ የቀበሌ ፣ የወረዳ ፣ የአውራጃ ፡ እና ፡ የክፍለ ፡ ሀገር ፡ ሥልጣኖችን ፡ የሚሠይሙበትን ፡ መርሕ ፡ ግብር ፡ ይፈጽማሉ ።

2.4.4 ፤ የቀበሌ ፡ አወቃቀር ፡ ገና ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ያልተዘረጋባቸው ፡ እንደ ፡ ኦጋዴን ፡ እና ፡ እንደ ፡ ቦረና ፡ ያሉ ፥ ነዋሪዎቻቸው ፡ በተለይ ፡ አርብቶ–ዐደሮች ፡ የኾኑባቸው ፡ አካባቢዎች ፥ አብዛኛዎቹን ፡ ነዋሪዎች ፡ በሚያሳትፍ ፡ ባህላዊ ፡ የውክልና ፡ ዘዴ ፡ ተወካዮቻቸውን ፡ በውዴታዊ ፡ አገባብ ፡ ሊሠይሙ ፡ ይችላሉ ።

2.4.5 ፤ **የኢትዮጵያን** ፡ ክፍላተ ፡ ሀገር ፡ **ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ የውንብድና ፡ ይዘት** ፡ ነጻ ፡ የማውጣቱ ፡ ኺደት ፡ በነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ አብላጫውን ፡ **የኢትዮጵያ** ፡ ክፍሎች ፡ ሲያዳርስ ፥ **ኢ.ህ.ሥ.አ.** ፡ ሀገራዊውን ፡ **የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት** ፡ አቋቁሞ ፥ አካባቢውን ፡ የማስተዳደር ፡ እና ፡ **የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ የውንብድና ፡ ይዘትን** ፡ በገቢር ፡ በማስወገድ ፡ **የኢትዮጵያን** ፡ ዐዲስ ፡ **ክዋኔ** ፡ በመላ ፡ **ኢትዮጵያ** ፡ የመከወን ፡ ተግባርን ፡ እስከ ፡ ፍጻሜው ፡ ይቀጥላል ፤ ለዚህም ፡ ተግባሩ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ያውለው ፡

---

4 የ"ዐውደ ፡ ቀለም" ፡ መርበቢያ ፦ http://www.awde-qelem.net

ዘንድ ፥ ከሕዝቡ ፡ የዓሥራት ፡ (10%) ፡ ግብርን ፡ የመሰብሰብ ፡ መብት ፡ እና ፡ ሥልጣን ፡ ይኖረዋል ።

2.4.6 ፤ በውድም ፡ ኾነ ፡ በግድ ፡ ከሥልጣኑ ፡ ሰገነት ፡ የሚወርዱት ፡ **የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ የውንብድና ፡ ይዘት** ፡ ኀላፊዎች ፡ እና ፡ ሹማምት ፥ **የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት** ፡ ወቅት ፡ አክትሞ ፡ በቋሚው ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንግሥት** ፡ እስኪተካ ፡ ድረስ ፥ በቁም ፡ እስርንት ፡ ቈይተው ፥ ዐዲሱ ፡ መንግሥት ፡ ሲቋቋም ፥ ጕዳያቸው ፡ በቋሚው ፡ ሀገራዊ ፡ የፍትሕ ፡ ችሎት ፡ ፍጻሜውን ፡ ያገኛል ።

2.4.7 ፤ ኾኖም ፥ በከባድ ፡ እና ፡ በተመሰከረ ፡ **የሀገር ፡ ክዳት** ፣ **የኢሰብአዊ ፡ ድርጊት** ፣ **የነፍስ ፡ ማጥፋት** ፣ **የሀገር ፡ ሀብትን ፡ የመመዝበር ፡ እና ፡ የማስመዝበር ፡ የሙስና ፡ ወንጀሎች** ፡ የሚከሰሱ ፡ ኀላፊዎችም ፡ ኾኑ ፡ ተርታዎች ፡ ሰዎች ፥ ጕዳያቸው ፡ የመሸጋገሪያው ፡ መንግሥት ፡ በሚያስችለው ፡ የፍርድ ፡ ችሎት ፡ ታይቶ ፥ በሽግግሩ ፡ ወቅት ፡ ፍትሓዊ ፡ ፍጻሜውን ፡ ያገኛል ።

2.4.8 ፤ **የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ የውንብድና ፡ ይዘት** ፡ ኀላፊዎች ፥ **የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት** ፡ ምሥረታን ፡ በግድ ፡ ብቻ ፡ የሚቀበሉት ፡ ኾነው ፡ ስለተገኙ ፥ ይሀ ፡ ዐመፀኛነታቸው ፡ በሕዝብ ፡ እና ፡ በ**ሀገር** ፡ ላይ ፡ ነውና ፥ በፍርድ ፡ ችሎት ፡ አንጻር ፡ ከ**ሀገር ፡ ክዳት ፡ ወንጀል** ፡ ስለሚቈጠርባቸው ፥ አንዳች ፡ አስተያየት ፡ ሳይደረግላቸው ፥ ዐይነተኛ ፡ እና ፡ አስተማሪ ፡ ብይንን ፡ ያስበይንባቸዋል ።

## 2.5 ፤ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ መቼ ፧

2.5.1 ፤ **የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ የውንብድና ፡ ይዘት** ፥ በፀረ ፡ ሀገር ፡ የጦርነት ፡ ድርጊቱ ፡ ራሱን ፡ ከመሸጋገሪያው ፡ መንግሥት ፡ ምሥረታ ፡ ኺደት ፡ ወግዷል ።

2.5.2 ፤ **የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ የውንብድና ፡ ይዘት** ፡ **የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት** ፡ መቋቋምን ፡ ከመሠረቱ ፡ የማይደግፈው ፡ ሐሳብ ፡ ኾኖ ፡ ከመረጋገጡም ፡ የባሰ ፥ በሕዝብ ፡ እና ፡ በሀገር ፡ ላይ ፡ ጦርነትን ፡ በማወጁ ፡ ምክንያት ፥ የውንብድና ፡ ይዘቱ ፡ በኀይል ፡ እና ፡ በግዴታ ፡ እንዲወገድ ፡ ይደረጋል ።

2.5.3 ፤ **የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ የውንብድና ፡ ይዘት** ፡ ከመወገዱ ፡ በፊት ፡ ከ 50% ፡ በላይ ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፡ ነጻ ፡ እወጡ ፡ ወረዳዎች ፡ ውስጥ ፡ መኖሩ ፡ ሲረጋገጥ ፥ **የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት** ፡ ምሥረታ ፡ ሊከናወን ፡ ይችላል ፤ **መንበሩንም** ፡ በሀገር ፡ ውስጥ ፥ እተመቸው ፡ ቦታ ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል ።

## 2.6 ፤ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ እስከ ፡ መቼ ፧

2.6.1 ፤ **የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት** ፡ ከተቋቋመ ፡ ከ 6 ፡ ወር ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ በሚፈጅ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፥ **የኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ** ፡ በሙሉ ፡ ነጻነት ፡ መክሮ ፡ እና ፡ ዘክሮ ፥ **በሥልጡንሕዝባዊ** ፡ መንገድ ፡ አጠናቅቆ ፡ በድምፅ ፡ ያጸደቀውን ፡ ረቂቅ ፡ **ክዋኔ** ፡ (ወይም ፡ ረቂቅ ፡ **ሕገ ፡ መንግሥት**) ፥ **የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥቱ** ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ ባልበለጠ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ለሕዝብ ፡ ፈረዳ ፡ ያቀርበዋል ።

2.6.2 ፤ ለሕዝብ ፡ ፈረዳ ፡ የቀረበው ፡ ረቂቅ ፡ **ክዋኔ** ፡ በሕዝብ ፡ አብላጫ ፡ ድምፅ ፡ (>50%) ፡ ሲጸድቅ ፥ ሦስት ፡ ወር ፡ በማይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፥ በዐዲሱ ፡ **ክዋኔ** ፡ መሠረት ፡ ሀገራዊ ፡ ምርጫ ፡ ተካኺዶ ፥ የምርጫው ፡ ውጤት ፡ እንደታወቀ ፥ የመሸጋገሪያው ፡ መንግሥት ፡ ሥልጣኑን ፡ ዐዲስ ፡ ለተሠየመው ፡ አሸናፊ ፡ ወገን ፡ በደንቡ ፡ መሠረት ፡ አስረክቦ ፡ እና ፡ ኀላፊነቱን ፡ ተወጥቶ ፡ ከ**ኢትዮጵያ** ፡ የሥልጣን ፡ ሰገነት ፡ ይወርዳል ።

2.6.3 ፤ ለሕዝብ ፡ ፈረዳ ፡ የቀረበው ፡ ረቂቅ ፡ **ክዋኔ** ፡ የሕዝብን ፡ አብላጫ ፡ ድምፅ ፡ ባያገኝ ፡ ግን ፡ (<50%) ፥ ረቂቅ ፡ **ክዋኔው** ፡ **በኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ** ፡ ዳግም ፡ ተመክሮበት ፡ እና ፡ ተሻሽሎ ፥ ሦስት ፡ ወር ፡ በማያልፍ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ **ለሕዝባዊ ፡ ፈረዳ** ፡ ዳግም ፡ ይቀርባል ። ይህም ፡ የማሻሻያ ፡ ኺደት ፡ የሚፈለገውን ፡ ያኽል ፡ ሊደጋገም ፡ ይችላል ።

## ምዕራፍ ፡ 3 ፤

## የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እግዚእና ፡ ይከበራል ።

### 3.1 ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የእግዚእና ፡ መብት ።

3.1.1 ፤ **የኢትዮጵያ** ፡ አንድያ ፡ ባለቤት ፡ መሳው ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፡ ነውና ፥ በውስጥም ፡ በውጭም ፡ ከ**ኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፡ እና ፡ ከሕገኞች ፡ ወኪሎቹ ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ በ**ኢትዮጵያ** ፡ **ክዋኔ** ፡ ረገድ ፡ አንዳች ፡ የውሳኔ ፡ መብት ፡ አይኖረውም ። **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፡ እና ፡ **ሕጋውያን ፡ ተወካዮቹ** ፡ የ**ኢትዮጵያ** ፡ **ሀገራዊ ፡ እግዚእና** ፡ አንድያ ፡ ባለመብቶች ፡ ናቸው ።

3.1.2 ፤ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፥

- እንደራሴዎቹን ፡ በሙሉ ፡ ነጻነት ፡ እና ፡ በውዴታው ፡ ሲወክል ፥
- በእነርሱም ፡ አማካይነት ፡ የጋራ ፡ ፈቃዱ ፡ የኾነውን ፡ **ክዋኔውን** ፡ (ሕገ ፡ መንግሥቱን) ፡ በ**ሕዝባዊ ፡ ፈረዳው** ፡ አጽድቆ ፡ የርትዕ ፡ ኹነቱን ፡ ሲከውን ፥
- በ**ክዋኔውም** ፡ መሠረት ፡ ሀገራዊ ፡ ምርጫ ፡ ተካኺዶ ፡ ዐዲሱ ፡ **ሥልጡንሕዝባዊ** ፡ መንግሥት ፡ የግዛት ፡ ሥልጣኑን ፡ ለተወሰነለት ፡ ዘመን ፡ ሲረከብ ፥

ያን ፡ ጊዜ ፥ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፡ **እግዚእና** ፡ መከበሩ ፡ ይረጋገጣል ።

### 3.3 ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በእግዚእናው ፡ ከሠራው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ክዋኔ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ክዋኔ ፡ አይኖርም ።

3.3.1 ፤ ዐዲሱ ፡ **የኢትዮጵያ** ፡ **ክዋኔ** ፡ የመንግሥታውያን ፡ የሥልጣን ፡ ክፍሎች ፣ ያስተዳደር ፡ ተዋረዶች ፣ የግዛት ፡ ዕርከኖች ፣ የዘርፍ ፡ ድርጅቶች ፡ እና ፡ ተቋማት ፡ መቋቋሚያ ፡ አንድያ ፡ ሕጋዊ ፡ ምንጫቸው ፡ ይኾናል ።

3.3.2 ፤ ዐዲሱ ፡ **የኢትዮጵያ** ፡ **ክዋኔ** ፡ ለመንግሥቱ ፡ ውሳኔዎች ፡ እና ፡ ክንዋኔዎች ፡ ኹሉ ፡ አንድያ ፡ ሕጋዊ ፡ መሠረታቸው ፡ ይኾናል ።

3.3.3 ፤ የቀደሙ ፡ ሕጎች ፣ ዐዋጆች ፣ ደንቦች ፣ ማዘዣዎች ፣ ስምምነቶች ፣ ወዘተርፈ ፡ ... ፥ ዐዲሱን ፡ **ክዋኔ** ፡ በቃሉም ፣ በመንፈሱም ፣ በይዞታውም ፡ እስካልተፃረሩት ፡ ድረስ ፥ ተፈጻሚዎች ፡ ይኾናሉ ።

3.3.4 ፤ የቀደሙ ፡ ሕጎች ፣ ዐዋጆች ፣ ደንቦች ፣ ማዘዣዎች ፣ ስምምነቶች ፣ ወዘተርፈ ፡ ... ፥ ዐዲሱን ፡ **ክዋኔ** ፡ ወይ ፡ በቃሉ ፣ ወይም ፡ በመንፈሱ ፣ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በይዞታው ፡ የሚፃረሩት ፡ ቢኾኑ ፡ ግን ፥ ማሻሻያ ፡ የሚደረግላቸው ፡ በሥርዐት ፡ ተሻሽለው ፡ እና ፡ በሕዝብ ፡ **ምክር ፡ ቤት** ፡ ጸድቀው ፣ ተፈጻሚዎች ፡ ይኾናሉ ። ማሻሻያ ፡ የማይገኝላቸው ፡ ደግሞ ፥ በሕዝብ ፡ **ምክር ፡ ቤት** ፡ ተሽረው ፡ ውድቆች ፡ ይኾናሉ ፤ እንዳስፈላጊነቱም ፡ ባዲስ ፡ ሕግ ፣ ወይ ፡ ዐዋጅ ፣ ወይ ፡ ደንብ ፣ ወይ ፡ ማዘዣ ፣ ወይ ፡ ስምምነት ፣ ... ፡ ይተካሉ ።

## ምዕራፍ ፡ 4 ፤

## የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የውክልና ፡ ኺደት ።

### 4.1 ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ የሀገራዊው ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ ፡ አባላት ፡ ኾነው ፡ የሚመክሩትን ፡ እንደራሴዎቹን ፡ ለመወከል ፥ በቀበሌ ፡ ደረጃ ፡ በሕዝባዊ ፡ ድምፅ ፡ አሰጣጥ ፡ ሥርዐት ፡ መርጦ ፡ የሚሠይማቸው ፡ ሦስት ፡ ሦስት ፡ ሥዩማን ፥

በወረዳ ፡ ደረጃ ፡ ተሰብስበው ፥ ከመካከላቸው ፡ የወረዳውን ፡ ሦስት ፡ ዕጩዎች ፡ ይሠይማሉ ።

4.2 ፤ **ለሀገራዊው ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ** ፡ የሚሠየሙት ፡ የወረዳ ፡ ተወካዮች ፡ ብዛት ፡ በወረዳው ፡ የነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ መሠረት ፥ ለ 200 ፡ ሺሕ ፡ ነዋሪዎች ፡ አንድ ፡ ተወካይ ፡ በሚል ፡ ምጣኔ ፡ ይኾናል ።

4.3 ፤ የወረዳው ፡ የነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ ከ 200 ፡ ሺሕ ፡ ቢያልፍ ፥ ለተጨማሪ ፡ አንድ ፡ ተወካይ ፥ ከ 100 ፡ ሺሕ ፡ እስከ ፡ 200 ፡ ሺሕ ፡ ተጨማሪ ፡ የነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ መኖር ፡ አለበት ።

4.4 ፤ ከ 150 ፡ ሺሕ ፡ ነዋሪዎች ፡ በታች ፡ ያሉት ፡ ወረዳ ፥ ካጎራባች ፡ ወረዳ ፡ ጋራ ፡ ተዳምሮ ፥ የተወካዮቻቸው ፡ መጠን ፡ በነዋሪዎቻቸው ፡ ብዛት ፡ መሠረት ፡ ይወሰናል ።

4.5 ፤ እስከ ፡ 200 ፡ ሺሕ ፡ ነዋሪዎች ፡ ያሉት ፡ ወረዳ ፥ ከቀበሌዎቹ ፡ ከተውጣጡት ፡ ተወካዮች ፡ ውስጥ ፡ 3 ቱን ፡ መርጦ ፥ አብላጫ ፡ ድምፅ ፡ ያገኘውን ፡ ተወካይ ፥ የወረዳው ፡ እንደራሴ ፡ አድርጎ ፡ **ለሀገራዊው ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ** ፡ አባልነት ፡ ይወክላል ። ቀሪዎቹን ፡ ኹለት ፡ ተወካዮች ፡ በተጠባባቂነት ፡ መዝግቦ ፥ **በወረዳው ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር** ፡ በሊቀ ፡ መንበርነት ፡ እና ፡ በምክትል ፡ ሊቀ ፡ መንበርነት ፡ ይሠይማቸዋል ።

4.5.1 ፤ በወረዳው ፡ ቀበሌዎች ፡ ኹሉ ፡ የተሠየሙት ፡ ሦስት ፡ ሦስት ፡ ሥዩማን ፥ በመዋቅራዊው ፡ ሰነድ ፡ መሠረት ፥ **የወረዳውን ፡ ምክር ፡ ቤት** ፡ ይመሠርታሉ ፤ ሊቀ ፡ መንበራቸውንና ፡ **የወረዳውን ፡ ምክር ፡ ቤት** ፡ ኀላፊዎች ፡ ይሠይማሉ ።

4.5.2 ፤ የወረዳው ፡ **ፈጻሚ ፡ ምክር** ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፥ **በመዋቅራዊው ፡ ሰነድ** ፡ መሠረት ፥ **የወረዳውን ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር** ፡ የሥራ ፡ ኀላፊዎች ፡ **ለወረዳው ፡ ምክር ፡ ቤት** ፡ አቅርቦ ፡ ያስጸድቃል ።

4.5.3 ፤ **የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት** ፡ በሀገር ፡ ደረጃ ፡ ሲዋቀር ፥

4.5.3.1 ፤ **የወረዳ ፡ ምክር ፡ ቤቱን** ፡ ሥራ ፡ እና ፡ **የወረዳ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክሩን** ፡ ሥራ ፡ ሕጋዊነት ፡ የሚቈጣጠር ፥ እንዲሁም ፡ በኹለቱ ፡ አካላት ፡ መካከል ፡ የሚኖረውን ፡ ሱታፌ ፡ የሚመግብ ፡ አንድ ፡ **የወረዳ ፡ አስተዳዳሪ** ፡ ሠይሞ ፡ ይልካል ፤

4.5.3.2 ፤ በወረዳው ፡ ሕግ ፡ እና ፡ ሰላም ፡ እንዲሰፍን ፥ **የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤትንና ፡ የወረዳ ፡ ሕግ ፡ አስከባሪ ፡ ኀይልን** ፡ ያቋቁማል ።

4.6 ፤ እንዳስፈላጊነቱ ፥ ወረዳዎች ፡ ኹሉ ፡ ተመጣጣኝ ፡ የነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ እንዲኖራቸው ፥ የመሸጋገሪያው ፡ መንግሥት ፡ ወረዳዎችን ፡ በማሸጋሸግ ፥ የማስተካከያ ፡ ክፍፍል ፡ ሊያደርግ ፡ ይችላል ።

4.7 ፤ ከመላ ፡ **ኢትዮጵያ** ፡ ወረዳዎች ፡ ተወክለው ፡ የተውጣጡት ፡ አባላት ፥ የ**ኢትዮጵያ**ን ፡ ዐዲስ ፡ **ክዋኔ ፡ (ሕገ ፡ መንግሥት)** ፡ የሚከውነው ፡ **የሀገራዊው ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ** ፡ አባላት ፡ ኾነው ፡ በወግ ፡ ይሠየማሉ ።

## ምዕራፍ ፡ 5 ፤

## የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ አመሠራረት ፡ እና ፡ ተግባር ።

5.1 ፤ **ሕጋጊ ፡ ሥልጣን** ።

5.1.1 ፤ **ሀገራዊው ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ** ፥ ከእየወረዳው ፡ ተወክለው ፡ በመጡ ፡ የሕዝብ ፡ እንደራሴዎች ፡ ይሠየማል ።

5.1.2 ፤ **ሀገራዊው ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ** ፥ **የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥቱን** ፡ **ሕጋጊ ፡ ሥልጣን** ፡ ይይዛል ።

5.1.3 ፤ **ሀገራዊው ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ** ፥ አርቅቆ ፡ ያጸደቀውን ፡ ዐዲሱን ፡ የ**ኢትዮጵያ** ፡ ረቂቅ ፡ **ክዋኔ** ፡ **ለሕዝባዊ ፡ ፈረዳ** ፡ አቅርቦ ፡ በ**ኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፡ ያስጸድቃል ።

5.1.4 ፤ **ሀገራዊው ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ** ፥ **የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥቱን** ፡ ሕግጋት ፡ ኹሉ ፡

ይወስናል ።

5.1.5 ፤ **ሀገራዊው ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ** ፥ **የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥቱን** ፡ **ፈጻሚ ፡ ምክር** ፡ **ሊቀ ፡ መንበር** ፡ **በጊዜያዊ ፡ ርእሰ ፡ ሀገርነት** ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ይሠይማል ። (የጥቈማው ፡ እና ፡ የምርጫው ፡ ዝርዝር ፡ ክንዋኔ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይፋ ፡ በሚወጣው ፡ **መዋቅራዊ ፡ ሰነድ** ፡ ይገለጻል ። )

5.1.6 ፤ **ሀገራዊው ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ** ፥ **የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥቱ** ፡ **ፈጻሚ ፡ ምክር** ፡ **ሊቀ ፡ መንበር** ፡ የሚያቀርብለትን ፡ ያስተዳደሩን ፡ **መጋብያን** ፡ ወይም ፡ "ሚኒስትሮች" ፡ ዝርዝር ፡ ተመልክቶ ፥ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ያጸድቃል ።

5.1.7 ፤ **ሀገራዊው ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ** ፥ **የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥቱን** ፡ **ፈጻሚ ፡ ምክር** ፡ የማይተማመንበት ፡ ኾኖ ፡ ቢያገኘው ፥ በጕዳዩ ፡ ድምፅ ፡ ሰጥቶበት ፥ በ2/3ኛ ፡ ድምፅ ፡ ብልጫ ፡ **የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥቱን** ፡ **ፈጻሚ ፡ ምክር** ፡ ሊሽረውና ፥ በአንቀጽ ፡ 5.1.5 ፡ እና ፡ አንቀጽ ፡ 5.1.6 ፡ *መሠረት* ፥ ሌላ ፡ **የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት** ፡ **ፈጻሚ ፡ ምክርን** ፡ ሳምንት ፡ በማያልፍ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ሊሠይም ፡ ይችላል ።

5.1.8 ፤ **ሀገራዊው ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ** ፥ የፈጻሚውን ፡ ሥልጣን ፡ እና ፡ የፈታሒውን ፡ ሥልጣን ፡ ሥራዎች ፡ ሕጋዊነት ፡ ይቈጣጠራል ።

## 5.2 ፤ ፈጻሚ ፡ ሥልጣን ።

5.2.1 ፤ **ጊዜያዊ ፡ ርእሰ ፡ ሀገሩ** ፥ ከተሠየመ ፡ ሳምንት ፡ በማያልፍ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ጠቅላይ ፡ መጋቢውን ፡ እና ፡ የእየምግብናውን ፡ መጋቢዎች ፡ መርጦ ፡ በ**ሀገራዊው ፡ ፈጻሚ** ፡ **ምክር** ፡ አባልነት ፡ ሹመታቸው ፡ የስም ፡ ዝርዝራቸውን ፡ ለ**ሀገራዊው ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ** ፡ አቅርቦ ፡ ያስጸድቃል ።

5.2.2 ፤ **ሀገራዊው ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር** ፥ **የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥቱን ፡ ፈጻሚ** ፡ **ሥልጣን** ፡ ይይዛል ።

5.2.3 ፤ ለመጋቢነት ፡ (ለ"ሚኒስትርነት") ፡ የሚታጩት ፡ እና ፡ የሚሠየሙት ፡ ባለሥልጣኖች ፥ *መንግሥታውያን* ፡ ኀላፊነቶች ፡ በሕግ ፡ ሊሰጧቸው ፡ የሚገባቸው ፡ **ኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራውያን** ፡ መኾን ፡ አለባቸው ።

5.2.4 ፤ ለመጋቢነት ፡ (ለ"ሚኒስትርነት") ፡ የሚታጩት ፡ እና ፡ የሚሠየሙት ፡ ባለሥልጣኖች ፥ **የሀገራዊው ፡ ከዋኝ ፡ ምክር** ፡ አባላት ፡ ሊኾኑም ፡ ላይኾኑም ፡ ይችላሉ ።

## 5.3 ፤ ፈታሒ ፡ ሥልጣን ።

5.3.1 ፤ በዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ እና ፡ ኀላፊነት ፡ ያሉ ፡ የሕግ ፡ ባለሚያዎች ፥ በሥልጣን ፡ ብልግና ፣ በሙስና ፡ እና ፡ በመሳሰሉ ፡ ወንጀል ፡ ከቀደሙ ፡ ይዘቶች ፡ ጋራ ፡ በወንጀል ፡ ያልተነካኩ ፡ ተለይተው ፡ **በፈታሒው ፡ ሥልጣን** ፡ ዕርከኖች ፡ ተመድበው ፥ ሥልጣናቸው ፡ በ**ሀገራዊው** ፡ **ከዋኝ ፡ ጉባኤ** ፡ ይጸድቅላቸዋል ።

5.3.2 ፤ **ሀገራዊው ፡ ፈታሒ ፡ ምክር** ፥ **የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥቱን ፡ ፈታሒ** ፡ **ሥልጣን** ፡ ይይዛል ። (የሀገራዊው ፡ ፈታሒ ፡ ምክር ፡ አሰሠያየም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይፋ ፡ በሚወጣው ፡ **መዋቅራዊ ፡ ሰነድ** ፡ ይገለጻል ። )

5.3.3 ፤ እንዳስፈላጊነቱ ፥ ተጨማሪዎች ፡ ዐዳዲስ ፡ የሕግ ፡ ባለሚያዎች ፡ በፍትሕ ፡ ምጋቤው ፡ ጠቋሚነት ፡ ለ**ሀገራዊው ፡ ከዋኝ** ፡ **ጉባኤ** ፡ ቀርበው ፥ የዳኝነት ፡ ሥልጣናቸው ፡ ጸድቆ ፥ በዳኝነት ፡ ሊመደቡ ፡ ይችላሉ ።

5.3.4 ፤ ተፈላጊዎቹ ፡ **የፈታሒው ፡ ሥልጣን** ፡ *መጣራት* ፡ እና ፡ *መጕልበት* ፡ በፍትሕ ፡ ምጋቤው ፡ ትልም ፡ እና ፡ በ**ሀገራዊው** ፡ **ፈታሒ ፡ ምክር** ፡ ይኹንታ ፡ ይከናወናሉ ።

5.3.5 ፤ ፈታሒው ፡ ሥልጣን ፥ የፈጻሚውን ፡

ሥልጣን ፡ እና ፡ የሐጋጊውን ፡ ሥልጣን ፡ ሥራዎች ፡ ሕጋዊነት ፡ ይቈጣጠራል ፤ በኹለቱም ፡ ሥልጣናት ፡ መኻከል ፡ በሚኖረው ፡ ሱታፌ ፡ አንዳች ፡ አለመግባባት ፡ ወይም ፡ ውዝግብ ፡ ቢፈጠር ፥ **ፈታሒው ፡ ሥልጣን** ፥ **ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ ችሎትን ፡ በማስቻል** ፥ ዳኝነቱን ፡ ይሰጣል ።

5.3.6 ፤ ማንኛውም ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፥ በመንግሥታዊ ፡ ኀላፊነቱ ፡ አንዳች ፡ በደል ፡ ቢፈጽም ፡ የሚከሰስበት ፥ ወይም ፡ አንዳች ፡ በደል ፡ ቢፈጸምበት ፡ የሚከስበት ፡ **አስተዳደራዊ ፡ ፍርድ ፡ ቤት** ፡ ይቋቋማል ።

## 5.4 ፤ የስያስ ፡ ቡድኖች ።

5.4.1 ፤ **የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ የውንብድና ፡ ይዘት** ፡ "ገገር ፡ ፓርቲ" ፡ እና ፡ ተሳታፊዎች ፡ "ፓርቲዎች" ፡ የአመራር ፡ አባላት ፡ በጠቅላላው ፥ በየትኛውም ፡ **የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት** ፡ የሥልጣን ፡ ክፍልም ፡ ኾነ ፡ ዕርከን ፡ አይሠየሙም ።

5.4.2 ፤ በኀላፊነት ፡ ያሉ ፡ የሌሎች ፡ ስያሳ ፡ ቡድኖች ፡ (ወይም ፡ "የፖለቲካ ፡ ፓርቲዎች") ፡ አመራር ፡ አባላት ፡ በየትኛውም ፡ **የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት** ፡ የሥልጣን ፡ ክፍልም ፡ ኾነ ፡ ዕርከን ፡ አይሠየሙም ። የሚሠየሙ ፡ ቢኖሩ ፥ አስቀድመው ፡ ከቡድናቸው ፡ ኀላፊነታቸው ፡ መውረድ ፡ ይኖርባቸዋል ።

## 5.5 ፤ የጦር ፡ እና ፡ የጸጥታ ፡ ኀይሎች ።

5.5.1 ፤ **የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ የውንብድና ፡ ይዘትን** ፡ በኀይል ፡ ገርስሶ ፡ ለመጣል ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በተደረገው ፡ **የዐርበኝነት ፡ ትግል** ፥ ከፍተኛ ፡ መሥዋዕትነትን ፡ በመክፈል ፡ **በፋኖ** ፡ **ሀገራዊ** ፡ **ኀይልነት** ፡ እና ፡ በማንኛውም ፡ **ኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊ ፡ ኀይልነት** ፡ ተደራጅተው ፡ ለድል ፡ ያበቁ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ ዕውቅና ፡ በመስጠት ፥ ከተገቢው ፡ ምስጋና ፡ እና ፡ ሽልማት ፡ ጋራ ፥ ለተከፈለው ፡ የሕይወት ፡ እና ፡ የአካል ፡ መሥዋዕትነት ፣ የጊዜ ፡ እና ፡ የንብረት ፡ ክሳራ ፡ ተገቢው ፡ ካሳ ፡ ኹሉ ፡ በመሸጋገሪያው ፡ መንግሥት ፡ ወቅት ፡ ተለይቶ ፡ እና ፡ ታስቦ ፡ በመላ ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፡ ስም ፡ በክብር ፡ ይበረከትላቸዋል ።

5.5.2 ፤ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ለድል ፡ ያበቁት ፡ የትጥቅ ፡ ትግል ፡ ድርጅቶች ፡ አባላት ፥ እንደእየፈቃዳቸው ፡ እና ፡ እንደእየችሎታቸው ፥ ወታደራዊ ፡ አገልግሎታቸውን ፡ በቋሚነት ፡ ሊቀጥሉ ፡ ባለ ፡ ሙሉ ፡ መብት ፡ ናቸው ። ፈቃዳቸው ፡ የኾነላቸውም ፥ ኹኔታቸው ፡ እየተመረመረ ፥ ተፈላጊው ፡ ሥልጠና ፡ እና ፡ ምደባ ፡ እየተደረገላቸው ፥ በቋሚዎቹ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የጦር ፣ የጸጥታ ፡ እና ፡ የሕግ ፡ አስከባሪ ፡ ኀይሎች ፡ ውስጥ ፡ ተቀጥረው ፡ የማገልገል ፡ መብታቸው ፡ ይከበርላቸዋል ።

5.5.3 ፤ **የኢትዮጵያ** ፡ የምድር ፡ ኀይል ፣ የአየር ፡ ኀይል ፣ የባሕር ፡ ኀይል ፥ እንዲሁም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሕግ ፡ አስከባሪ ፡ እና ፡ የጸጥታ ፡ ኀይሎች ፥ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ በመሸጋገሪያው ፡ መንግሥት ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ይኾናሉ ።

5.5.4 ፤ በተሻረው ፡ "ክልላዊ" ፡ መዋቅር ፡ መሠረት ፡ ተቋቁመው ፡ የነበሩት ፡ "ልዩ ፡ ኀይሎች" ፡ እና ፡ "የክልል ፡ ፖሊሶች" ፡ ኹሉ ፡ ተሽረው ፥ ከሰው ፡ ኀይላቸው ፡ የተወሰነው ፡ ወደ ፡ ሀገራዊው ፡ ሰራዊት ፡ ሲጠቃለል ፥ ቀሪው ፥ ተጨማሪ ፡ ሥልጠና ፡ እና ፡ ርዳታ ፡ እየተሰጠው ፥ ወደ ፡ ሰላማዊ ፡ ኑሮው ፡ ይመለሳል ።

5.5.5 ፤ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያት ፥ በዐመፃ ፡ ግብር ፡ ተሰማርተው ፡ ለኖሩ ፡ ኀይሎች ፡ ተርታ ፡ አባላት ፥ የምሕረት ፡ ዐዋጅ ፡ ይታወጃል ። በምሕረት ፡ ዐዋጁ ፡ መሠረት ፡

በሰላም ፡ ወደ ፡ መንግሥት ፡ የሚገቡት ፡ ወገኖች ፥ ሥልጠና ፡ እና ፡ ርዳታ ፡ እየተሰጣቸው ፥ ወደ ፡ ሰላማዊ ፡ ኑሯቸው ፡ ይመለሳሉ ።

5.5.6 ፤ በከባድ ፡ **የሀገር** ፡ ክዳት ፣ የሙስና ፡ እና ፡ የኢሰብአዊ ፡ ድርጊት ፡ ወንጀሎች ፡ ምክንያት ፡ የምሕረት ፡ ዐዋጁ ፡ የማይመለከታቸው ፡ አባላት ፡ ግን ፥

- በመንግሥት ፡ ቊጥጥር ፡ ሥር ፡ የሚገኙት ፡ ወዲያው ፡ ክስ ፡ ይመሠረትባቸዋል ፤
- እመንግሥት ፡ ቊጥጥር ፡ ሥር ፡ የማይገኙት ፥ በ**ሀገር** ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ተይዘው ፡ ለፍርድ ፡ ይቀርባሉ ፤
- ከ**ሀገር** ፡ ውጭ ፡ የሚገኙት ፡ ደግሞ ፥ በአህጉራውያን ፡ የሕግ ፡ ማስከበር ፡ ተቋማት ፡ አማካይነት ፡ ተይዘው ፡ በ**ሀገር** ፡ ውስጥ ፡ ለፍርድ ፡ ይቀርባሉ ።

## 5.6 ፤ የሀገራውያን ፡ ምልክቶች ፡ መስተካከል ።

5.6.1 ፤ **የኢትዮጵያ ፡ ሰንደቅ ፡ ዐላማ** ፡ ወደእነበረበት ፡ አረንጓዴ–ብጫ–ቀይ ፡ ሦስቱ ፡ ቀለማቱ ፡ እንዲመለስ ፥ በቀደመው ፡ **የውንብድና ፡ ይዘት** ፡ ተለጥፈውበት ፡ የነበሩት ፡ የፋሺዝም ፡ ምልክት ፡ ባላምስት ፡ እግር ፡ ብጫ ፡ ኮከብ ፡ እና ፡ ሰማያዊ ፡ መደብ ፡ ከሰንደቅ ፡ ዐላማው ፡ ይወገዳሉ ።

5.6.2 ፤ **የኢትዮጵያ ፡ ሰንደቅ ፡ ዐላማ** ፡ በዐዋጅ ፡ መሠረት ፡ እሚውለበለብበት ፡ ቦታ ፡ ኹሉ ፥ ሕጋዊው ፡ ሰንደቅ ፡ ዐላማ ፡ ብቻ ፡ ይውለበለባል ።

5.6.3 ፤ ከ**ኢትዮጵያ ፡ ሰንደቅ ፡ ዐላማ** ፡ በቀር ፥ ምንም ፡ ዐይነት ፡ የቀድሞ ፡ "ክልል" ፡ ኾነ ፡ የ"ፓርቲ" ፡ "ባንዲራዎች" ፡ በመንግሥታውያን ፡ ሕንጻዎች ፡ ላይ ፡ እና ፡ በሕዝብ ፡ አደባባይ ፡ አይውለበለቡም ።

5.6.4 ፤ ዐዲስ ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ መዝሙር** ፡ በሀገራዊ ፡ ውድድር ፡ ተመርጦ ፡ በመሸጋገሪያው ፡ መንግሥት ፡ ወቅት ፡ **በሀገራዊው ፡ ከዋኙ ፡ ጉባኤ ፡ ይጸድቃል ።**

5.6.5 ፤ **ዐማርኛ** ፡ አንድያው ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ ልሳን** ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፥ በመላ ፡ ሀገሪቱ ፡ አንድያው ፡ የመንግሥት ፡ የሥራ ፡ ቋንቋም ፡ ይኾናል ። አስፈላጊ ፡ በኾነባቸው ፡ አካባቢዎች ፡ ግን ፥ በመንግሥታውያን ፡ ያስተዳደር ፡ እና ፡ ያገልግሎት ፡ ተቋማት ፡ ውስጥ ፡ የአካባቢያውያን ፡ ቋንቋዎች ፡ የትርጕማ ፡ አገልግሎት ፡ ይሰጣል ።

# ምዕራፍ ፡ 6 ፤

## የመሸጋገሪያው ፡ መንግሥት ፡ ጠባይ ።

ባመሠራረቱ ፡ እና ፡ ባሠራሩ ፡–

- የሀገሪቱን ፡ ዐፄ ፡ ሥር ፡ ያከበረ ፡ ትውፊታዊ ፣
- ኹሉንም ፡ ሀገራዊ ፡ ያሳተፈ ፡ **ሥልጡንሕዝባዊ** ፣
- ለዐዲስ ፡ ሐሳብም ፡ የተከፈተ ፡ የርትዕ ፡ መከየድ ፡

ይኾናል ።

## 6.1 ፤ ባመሠራረት ፡ ረገድ ።

6.1.1 ፤ **ኢትዮጵያ** ፡ ጥንታዊት ፡ **ሀገር** ፡ ናትና ፥ ጥንት ፡ **ከዋኜዋ** ፡ (ዐፄ ፡ ሥሯ) ፡ እና ፡ ግዛታዊ ፡ ትውፊቷ ፡ ለዐዲሱ ፡ **ከዋኜዋ** ፡ መሠረት ፡ መኾናቸውን ፡ ኹሉም ፡ ወገኖች ፡ ይቀበላሉ ።

6.1.2 ፤ **ኢትዮጵያ** ፡ የእያንዳንዱ ፡ **ኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊ** ፡ የኾነችውን ፡ ያኽል ፥ እያንዳንዱ ፡ **ኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊም** ፡ የ**ኢትዮጵያ** ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፥ በእኩል ፡ **እግዚእና** ፥ በ**ሥልጡንሕዝባዊ** ፡ መንገድ ፡ ስለሀገሩ ፡ ዐዲስ ፡ **ከዋኜ** ፡ የመወሰን ፡ ሙሉ ፡ መብት ፡ ይኖረዋል ።

6.1.3 ፤ **የኢትዮጵያ ፡ ጥንተ ፡ ከዋኜ** ፡ ወይም ፡ **ዐፄ ፡ ሥር** ፡ መከበር ፡ እንደተጠበቀ ፡ ኾኖ ፥ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፥ በእግዚእናው ፡ መሠረት ፥ ለዐዲሱ ፡ የ**ኢትዮጵያ** ፡ **ከዋኜ** ፡ ይበጃል ፡ የሚለውን ፡ ዐዲስ ፡ ሐሳብ ፡ ኹሉ ፥

ስለ ፡ ርትዕነቱ ፡ መክሮ ፡ ዘክሮ ፡ ሲስማማበት ፥ ከዐዲሱ ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ክዋኔ** ፡ ጋራ ፡ በውዴታው ፡ ሊያዋሕደው ፡ ይችላል ።

6.1.4 ፤ **የኢትዮጵያ ፡ የእምነት ፡ ተቋማት** ፥ በተለይ ፡ ደግሞ ፥ **የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን** ፥ በታሪክ ፥ የሀገሪቱን ፡ ሥልጣኔ ፡ የጠበቁ ፡ እና ፡ የተከባከቡ ፡ እንደመኾናቸው ፡ መጠን ፥ በመሸጋገሪያው ፡ መንግሥት ፡ ወቅት ፥ በእየዕርከኑ ፡ ከምክሩ ፡ የሚሳተፉበት ፡ አገባብ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በጋራ ፡ ይወሰናል ።

6.1.5 ፤ ኢትዮጵያ ፥ ባለፉት ፡ ዘመናት ፥ እንደ ፡ "የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት" ፡ (ተ.መ.ድ.) ፡ ካሉ ፡ አህጉራውያን ፡ ድርጅቶች ፡ ጋራ ፡ የተፈራረመቻቸውን ፡ ስምምነቶች ፣ ውሎች ፣ ሥምረቶች ፣ ድንጋጌዎች ፡ ኹሉ ፤ በተለይ ፡ ደግሞ ፥ የሰብኣውያን ፡ መብቶች ፡ ድንጋጌዎችን ፡ ኹሉ ፡ በመሸጋገሪያው ፡ መንግሥት ፡ ወቅት ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ታከብራቸዋለች ። አንዳች ፡ ከሀገር ፡ ጥቅም ፡ ወይም ፡ ከሀገር ፡ ፈቃድ ፡ የሚፃረሩ ፡ ቢኖሩባቸው ፡ ግን ፥ የመሸጋገሪያው ፡ መንግሥት ፥ እንደ ፡ ኹኔታው ፥ ሊያሻሽላቸው ፥ አለዚያም ፡ ሊሽራቸው ፡ ይችላል ።

## 6.2 ፤ ባሠራር ፡ ረገድ ።

ከመደበኛ ፡ መንግሥታዊ ፡ ሥራ ፡ ጋራ ፥ መደበኛውን ፡ መንግሥታዊ ፡ ሥራ ፡ ለመደገፍም ፥ የሚከተሉት ፡ ድርገቶች ፣ ምድራጎች ፡ እና ፡ ተቋሞች ፡ በሦስቱም ፡ የሥልጣን ፡ ክፍሎች ፡ (**በፈጻሚው** ፣ **በሐጋጊው** ፡ እና ፡ **በፈታሒው** ፡ ሥልጣናት) ፡ በሕግ ፡ ይቋቋማሉ ።

6.2.1 ፤ **ኢትዮጵያ** ፡ አኹን ፡ እምትገኝበት ፡ የውድቀት ፡ ደረጃ ፡ እንድትዘቅጥ ፡ ለዘመናት ፡ የተፈጸሙባት ፡ ዐያሌ ፡ በደሎች ፡ አሉና ፥ እነዚህን ፡ በነቂስ ፡ የማረም ፡ እና ፡ የማስወገድ ፡ ቀዳምያን ፡ ሥራዎች ፡ ይሠራሉ ።

6.2.2 ፤ **ከኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ መንግሥት** ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ዘመናችን ፡ ድረስ ፡ በሕዝብ ፡ እና ፡ በ**ሀገር** ፡ ላይ ፡ በውስጥ ፡ እና ፡ በውጭ ፡ ኀይሎች ፡ የተፈጸሙ ፡ በደሎችን ፡ የሚመረምር ፡

**"ሀገራዊ ፡ የበደል ፡ እና ፡ የካሳ ፡ መርማሪ ፡ ድርገት"**

በፍትሕ ፡ ምጋቤ ፡ ኀላፊነት ፡ ይቋቋማል ።

6.2.3 ፤ **በሀገር** ፡ እና ፡ **በሕዝብ** ፡ ላይ ፡ በደልን ፡ በፈጸሙ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ክስን ፡ የሚመሠርት ፡ አንድ ፡

**"ሀገራዊ ፡ ክስ ፡ መሥራች ፡ ድርገት"**

በፍትሕ ፡ ምጋቤ ፡ ኀላፊነት ፡ ይቋቋማል ።

6.2.4 ፤ በደርግ ፡ የውንብድና ፡ አገዛዝ ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፡ ርስቱን ፡ አላግባብ ፡ ሲነጠቅ ፥ ይህም ፡ ንጥቂያ ፡ በ**ኢ.ፌ.ዴ.ሪ.** ፡ **የውንብድና ፡ አገዛዝ** ፡ ሲቀጥል ፥ የተፈለገው ፡ ዋነኛ ፡ ግብ ፡ ሕዝብን ፡ ከሀገሩ ፡ መንቀል ፡ እና ፡ መበተን ፡ ነበር ። ከዚያ ፡ ወዲህ ፥ በታሪክ ፡ ታይቶ ፡ የማይታወቅ ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ስደት ፡ ደረሰ ። በኢትዮጵያውያን ፡ ማኅበረሰቦችም ፡ ውስጥ ፡ በታሪክ ፡ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ከ**ሀገር** ፡ **ኢትዮጵያ** ፡ የመገንጠል ፡ ሐሳብ ፡ ሰሚን ፡ ማግኘት ፡ ዠመረ ። ርስት ፡ የ**ሀገር** ፡ እና ፡ የአንድነት ፡ አንዱ ፡ ማገር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ በውንብድና ፡ የተነጠቀ ፡ ሕጋዊ ፡ ርስት ፡ ኹሉ ፥ ***"ርስት ፡ በሺሕ ፡ ዓመቱ ፡ ለባለቤቱ"*** ፡ በሚለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ትውፊታዊ ፡ የፍትሕ ፡ መርሕ ፡ መሠረት ፥ **ለኢትዮጵያዊው ፡ ሀገራዊ** ፡ ባለርስት ፡ የሚመለስበትን ፡ ኹኔታ ፡ የሚያጠና ፡

**"የርስት ፡ አጣሪ ፡ ሀገራዊ ፡ ምድራግ"** ፡

በፍትሕ ፡ ምጋቤ ፡ ኀላፊነት ፡ ይቋቋማል ።

6.2.5 ፤ ከ 1966 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፡ የ**ሀገር** ፡

እና ፡ የ**ሕዝብ** ፡–

- **እግዚአናን** ፡ እና ፡ ነጻነትን ፡ ያስጣሱ ፡ እና ፡ ያስረመረሙ ፣
- ሀብትንና ፡ ንብረትን ፡ ያስመዘበሩ ፣
- ጥቅምንና ፡ ጸጋን ፡ ለባዕድ ፡ አሳልፈው ፡ ያሰጡ ፡

ሕግጋት ፣ ዐዋጆች ፣ ስምምነቶች ፣ ማዘዣዎች ፡ እና ፡ ውሎች ፣ አህጉራውያን ፡ ስምምነቶችም ፡ ተፈጽመዋል ። እነዚህን ፡ ፀረ ፡ ሀገር ፡ እና ፡ ፀረ ፡ ሕዝብ ፡ ሕግጋት ፣ ዐዋጆች ፣ ስምምነቶች ፣ ማዘዣዎች ፡ እና ፡ ውሎች ፡ መርምሮ ፡ የሚለይ ፡

**"የሀገራውያንና ፡ የአህጉራውያን ፡ ሕግጋት ፣ ደንቦች ፣ ስምምነቶች ፡ እና ፡ ዐዋጆች ፡ አጣሪ ፡ ምድራግ"** ፡

በፍትሕ ፡ ምጋቤ ፡ ኀላፊነት ፡ ይቋቋማል ፤ የምርመራውንም ፡ ውጤት ፡ ለ**ሀገራዊው ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ** ፡ ያቀርባል ።

6.2.6 ፤ ከ 1966 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፡ በተከታተሉት ፡ ፀረ ፡ ሀገር ፡ አገዛዞች ፥ ሀገራዊውን ፡ ልሳን ፡ ዐማርኛን ፡ ማጫጨት ፡ እንደ ፡ ዋና ፡ ግብ ፡ ተይዞ ፥ ሥርዐታዊ ፡ እና ፡ ተከታታይ ፡ በደል ፡ ተፈጽሞበታል ። የበደሉን ፡ ስፋት ፡ እና ፡ ጥልቀት ፡ መርምሮ ፥ ቋንቋውን ፡ ባጨረ ፡ ጊዜ ፡ ለመታደግ ፡ የሚያስችሉ ፡ ውሳኔዎችን ፡ የሚያጠና ፣ የዐማርኛን ፡ ግስ ፡ የሚያጠራ ፡ እና ፡ የሚያሟላ ፥ እንዲሁም ፡ የሀገር ፡ እና ፡ የቦታ ፡ ስመያዎችን ፡ ደንብ ፡ አርቅቆ ፡ ለ**ሀገራዊው ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ** ፡ የሚያቀርብ ፡

**"ሀገራዊ ፡ የግስ ፡ እና ፡ የስመያ ፡ ምድራግ"** ፡

በጠቅላይ ፡ መጋቢው ፡ ኀላፊነት ፡ ይቋቋማል ።

6.2.7 ፤ **ኢትዮጵያ** ፡ ዐዲሱን ፡ **ከዋኔዋን** ፡ ስትሠራ ፥ ግዛቷ ፡ ከቀበሌ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ **ሀገር** ፡ ደረጃ ፡ የሚዋቀርበትን ፡ የግዛት ፡ እና ፡ ያስተዳደር ፡ ድርጅት ፡ መርምሮ ፥ ለዘመኑ ፡ እና ፡ ለዘለቄታው ፡ የሚስማማውን ፡ የማሻሻያ ፡ ሐሳብ ፡ በጥናት ፡ መልክ ፡ ለ**ሀገራዊው ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ** ፡ የሚያቀርብ ፡

**"የግዛት ፡ እና ፡ ያስተዳደር ፡ አወቃቀር ፡ አጥኚ ፡ ድርገት"**

በጠቅላይ ፡ መጋቢው ፡ ኀላፊነት ፡ ይቋቋማል ።

6.2.8 ፤ **የኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ ድንበር** ፡ ዛሬ ፡ የሚገኝበትን ፡ ኹኔታ ፥ ከአህጉራውያን ፡ ውሎች ፡ እና ፡ ከታሪክ ፡ የተወረሱትን ፡ የሰነድ ፡ እና ፡ ሌሎች ፡ ማስረጃዎች ፡ አገናዝቦ ፡ የሚያጠና ፡ እና ፡ ውጤቱን ፡ ለ**ሀገራዊው ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ** ፡ የሚያገባ ፡

**"የዳር ፡ ድንበር ፡ መርማሪ ፡ ድርገት"**

በጠቅላይ ፡ መጋቢው ፡ ኀላፊነት ፡ ይቋቋማል ።

6.2.9 ፤ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ የሚቀናው ፡ በመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ የብቃት ፡ ደረጃም ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ማንኛውም ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ በሥራ ፡ ምድቡ ፡ ሊያሟላቸው ፡ የሚገቡትን ፡ ችሎታዎች ፡ የሚያጐናጽፈው ፡

**"የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ምድራስ"** ፡

በጠቅላይ ፡ መጋቢው ፡ ኀላፊነት ፥ በመዲናዋ ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ እና ፡ በክፍለ ፡ ሀገር ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ከተማዎች ፡ ይቋቋማል ።

6.2.10 ፤ ሀገራችን ፡ ብለው ፡ ተዘልለው ፡ ከሚኖሩበት ፡ አካባቢ ፡ በግፍ ፡ የተፈናቀሉ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ ወደእየቤታቸው ፡ የሚመልስ ፣ በደረሰባቸውም ፡ ጕዳት ፡ ዐይነት ፡ እና ፡ መጠን ፡ የሚክስ ፣ ይዞታቸውንም ፡ የሚያስመልስ ፥

**"የተፈናቃዮች ፡ ማቋቋሚያ ፡ ምድራግ"**

በጠቅላይ ፡ መጋቢው ፡ ኀላፊነት ፡ ተቋቁሞ ፥ ይሠራል ።

6.2.11 ፤ የኢትዮጵያን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ እና ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግጋትን ፡

ማሻሻያዎች ፡ የሚያመለክት ፥

**"የፍትሕ ፡ ሕግጋት ፡ ድርገት"**

በጠቅላይ ፡ መጋቢው ፡ ኀላፊነት ፡ ተቋቁሞ ፥ የጥናቱን ፡ ውጤት ፡ ለሀገራዊው ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ ፡ ያቀርባል ።

6.2.12 ፤ የኢትዮጵያን ፡ ምኅዳራዊ ፡ ደኅንነት ፡ የሚገመግም ፡ እና ፡ የብክለት ፡ ምንጮች ፡ የሚወገዱበትን ፡ አጠቃላይ ፡ ስልት ፡ የሚያመለክት ፥

**"የምኅዳራዊ ፡ ደኅንነት ፡ ምድራግ"**

በጠቅላይ ፡ መጋቢው ፡ ኀላፊነት ፡ ተቋቁሞ ፥ የጥናቱን ፡ ውጤት ፡ ለጠቅላይ ፡ መጋቢው ፡ ያቀርባል ።

6.2.13 ፤ የሀገር ፡ ቅርስ ፡ ጥበቃን ፣ ክብካቤን ፡ እና ፡ ምዝገባን ፡ የሚገመግም ፥

**"የሀገራዊ ፡ ቅርስ ፡ ድርገት"**

በጠቅላይ ፡ መጋቢው ፡ ኀላፊነት ፡ ተቋቁሞ ፥ የጥናቱን ፡ ውጤት ፡ ለጠቅላይ ፡ መጋቢው ፡ ያቀርባል ።

6.2.14 ፤ "የኢትዮጵያ ፡ አኃዛዊ ፡ ምድራግ"ን ፡ ("Ethiopian Statistical Agency")ን ፡ የመሳሰሉ ፡ መንግሥታውያን ፡ ተቋማትን ፡ የመረጃ ፡ አሰባሰብ ፣ አጠናቀር ፡ እና ፡ አሠራጨት ፡ ትኽክልነት ፡ የሚመረምር ፥

**"የመንግሥታዊ ፡ መረጃ ፡ መርማሪ ፡ ድርገት"**

በጠቅላይ ፡ መጋቢው ፡ ኀላፊነት ፡ ተቋቁሞ ፥ የጥናቱን ፡ ውጤት ፡ ለጠቅላይ ፡ መጋቢው ፡ ያቀርባል ።

## ምዕራፍ ፡ 7 ፤

## ዐዲሱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክዋኔ ፡ ባዲስ ፡ ሀገራዊ ፡ ኪዳን ፡ መሠረት ፡ ይከወናል ።

7.1 ፤ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፡ የጥንታዊት ፡ ሀገሩን ፡ **ኹነት** ፡ (መንግሥት) ፡ በዐዲሱ ፡ **ክዋኔው** ፡ ሲያድስ ፥ በሕዝቡ ፡ እና ፡ በርትዓዊ ፡ ኹነቱ ፡ መኻከል ፡ ለሚኖረው ፡ ሱታፌ ፡ ኸሉ ፡ ዐዲሱ ፡ **ክዋኔው** ፡ ዐዲሱ ፡ ሀገራዊ ፡ ኪዳኑ ፡ ይኾናል ።

7.2 ፤ ዐዲሱ ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ክዋኔ** ፡ በሚጸድቅበት ፡ ጊዜ ፥ ከ**ኢትዮጵያ** ፡ ወረዳዎች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያት ፡ ከሀገራዊው ፡ **ክዋኔ** ፡ ኺደት ፡ ያልተሳተፉ ፡ ወረዳዎች ፡ ቢኖሩ ፥ ከመሳተፍ ፡ የከለከላቸው ፡ ምክንያት ፡ እንደተወገደ ፥ በእነዚህ ፡ ቀሪዎች ፡ ወረዳዎች ፡ **ሕዝባዊ ፡ ፈረዳ** ፡ ተካኺዶባቸው ፥ በዐዲሱ ፡ **ክዋኔ** ፡ አንጻር ፡ አንዳች ፡ ቅርታ ፡ ወይ ፡ ተቃውሞ ፡ ቢኖራቸው ፥ ጉዳያቸው ፡ በቋሚው ፡ **የሕዝብ ፡ ምክር ፡ ቤት** ፡ (ወይም ፡ ሀገራዊ ፡ ሸንጎ) ፡ ታይቶ ፡ ይወሰናል ፨

**ጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፥**

**ኢ.ሀ.ሥ.አ. ።**

ተቀጥላ - 1 ፤

# የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ መሠረታዊ ፡ ሰነድ ።

መሠረታዊ ፡ ሰነድ_20111230

ነሐሴ ፡ 30 ፡ ቀን ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

# መሠረታዊ ፡ ሰነድ ።

(ቍ. ፡ 1 ፡ መሠረታዊ ፡ ሰነድን ፡ ዐድሶ ፡ እና ፡ አጽንቶ ፡ የተካ ። )

እኛ ፥ ከ**ኢትዮጵያ** ፥ ከእየኅብረተሰቡ ፡ መወለዳችን ፥ ከምድሯ ፥ ከእየግዛቱ ፣ ከእየከተማው ፡ እና ፡ ከእየቀበሌው ፡ መምጣታችን ፥ ሀገራችን ፡ **ኢትዮጵያን** ፥ መሳዋን ፡ ለመሠየም ፡ እና ፡ አንድነቷን ፡ ለመመሰል ፡ የፈቀደልን ፡ ***ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን*** ፤

- ነፍስ ፡ ወከፍ ፡ ባሕርያዊ ፡ መብታችንን ፡ እና ፡ ሕዝባዊ ፡ የገዢነት ፡ ሥልጣናችንን ፡ ለሚጠብቅልን ፡ ርትዓዊ ፡ ኹነቷ ፡ (የርትዕ ፡ መንግሥቷ) ፡ በመቆም ፥ በ**ኢትዮጵያ** ፡ **ሥልጣን ፡ ሰገነት** ፡ ላይ ፡ አላግባብ ፡ የወጣን ፡ ኀይል ፡ ኹሉ ፡ በመቃወም ፥ ያልተጨቈነ ፡ ኅሊናዋን ፡ ምርጫ ፡ ለመናገር ፥ ያልተገደደ ፡ ፈቃዷን ፡ ለመከተል ፡ ወደን ፤
- ሀገራዊ ፡ አንድነቷን ፡ የማጽናት ፥ ሐራነቷን ፡ የመጠበቅ ፥ **እግዚእናዋን** ፡ የማስከበር ፡ እና ፡ **ሥልጡንሕዝባዊ** ፡ የርትዕ ፡ ኹነቷን ፡ (የርትዕ ፡ መንግሥቷን) ፡ የማቆም ፡ ሀገራዊ ፡ ተግባራችንን ፡ ለመፈጸም ፡ ቈርጠን ፡ መነሣታችን ፥

በስሟ ፡ ለመወከል ፡ እና ፡ በሙሉ ፡ ሥልጣኗ ፡ ለመሥራት ፡ መብት ፡ የሚሰጠን ፡ ***ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን*** ፥ በቍ. ፡ 1 ፡ መሠረታዊ ፡ ሰነድ ፡ የተመለከተውን ፡ ዐድሰን ፡ እና ፡ አጽንተን ፥ የሚከተለውን ፡ ወስነን ፥ በስሟ ፡ ዐውጀናል ።

## ዐዋጅ ።

## አንቀጽ ፡ 1 ፤

## የኢትዮጵያ ፡ ኹነት ፡ እና ፡ አገዛዛዊ ፡ ፍልስፍና ።

1.1 ፤ በታሪኳ ፡ እንደተጻፈው ፥ **ኢትዮጵያ** ፥ በ 1260 ፡ ዓ.ም. ፡ ላይ ፥ መሳው ፡ ሕዝቧ ፥ በሕገኛዎቹ ፡ ወኪሎቹ ፡ ሰውነት ፥ በውዴታው ፡ ተሰብስቦ ፥ በነጻነት ፡ መክሮ ፡ እና ፡ ዘክሮ ፣ ወስኖ ፥ በቃል ፡ ኪዳኑ ፡ አጽንቶ ፥ በገቢር ፡ ባቈየው ፡ ደገኛ ፡ ዐፄ ፡ ሥሩ ፡ (ሥርዐተ ፡ መንግሥቱ) ፡ መሠረት ፥ እያንዳንዱ ፡ ሀገራዊ ፥ የብጤውን ፡ ባሕርያዊ ፡ መብት ፡ በማክበር ፡ ወንፈል ፥ በኅብረቱ ፡ የሠራት ፥ በፈቃዱ ፡ የከወናት ፥ አንዲት ፣ የማትከፋፈል ፡ እና ፡ **ሥልጡንሕዝባዊት** ፡ ሐራ ፡ **የርትዕ ፡ ኹነት** ፡ ናት ።

1.2 ፤ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፡ እግዚእ ፡ (ገዥ) ፡ ነው ። **ኢትዮጵያን** ፡ አኳኋኙ ፡ ሥልጣን ፥ ኳኋኙ ፡ ፈቃድ ፡ እና ፡ ኹኑ ፡ አካል ፥ ወይ ፡ ባንድ ፡ ቃል ፥ ምኳኑ ፥ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፡ እና ፡ የሰፈረበት ፡ ብሔር ፡ [ምድር] ፡ አንድነት ፡ ነው ። በሌላ ፡ አነጋገር ፥ አንጋሹ ፣ ነጋሹ ፡ እና ፡ መንግሥቱ ፥ ወይም ፡ ገዢው ፣ ተገዢው ፡ እና ፡ ግዛቱ ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፡ እና ፡ የብሔሩ ፡ [የምድሩ] ፡ አንድነት ፡ ነው ።

1.3 ፤ **የኢትዮጵያ ፡ ብሔር** ፥ በሦስቱም ፡ አኳያዎቹ ፥ በየብስም ፡ በባሕርም ፡ ባየርም ፥ በርትዓዊ ፡ መዋሐድ ፡ ከመስፋት ፡ በቀር ፥

የማይሸረፍ ፣ የማይቀነስ ፣ የማይጠብ ፡ ሙሉ ፡ ነው ።

1.4 ፤ **ኢትዮጵያ** ፡ አንዲት ፡ እና ፡ የማትከፋፈል ፡ **ሀገር** ፡ ናት ።

**አንቀጽ ፡ 2 ፤**

**የሥልጣን ፡ ተገቢነትን ፡ ስለ ፡ ማረጋገጥ ።**

2.1 ፤ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፥ ከማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ የበለጠ ፡ ባስተባበረው ፡ እና ፡ ባስፋፋው ፡ የየካቲት ፡ ወር ፡ 1966 ፡ ዓ.ም. ፡ ሀገራዊ ፡ ንቅናቄው ፡ ኀይል ፥ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ የያዙበትን ፡ የግዛት ፡ መብቱን ፡ በሰላም ፡ ሲያስመልስ ፥ ሳዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ሰጥታ ፡ የተሰማሩትን ፡ ሰራዊቶች ፡ ለማስተባበር ፡ የተመደበው ፡ ወቷደራዊ ፡ ደርግ ፤

2.1.1 ፤ ሊጠብቀው ፡ የቆመለትን ፡ ሕዝብ ፡ ከድቶ ፥ የተውጣጣባቸውን ፡ ደንቦች ፡ አታሎ ፥ ከርክክቡ ፡ መኻከል ፡ ሥልጣኑን ፡ በውንብድና ፡ አስጥሎ ፥ የትግሉን ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ አጨናግፏል ፥ የንቅናቄውንም ፡ ደኅኛ ፡ ጉዞ ፡ አቋርጧል ፤

2.1.2 ፤ ለፍትሕ ፡ ችሎት ፡ እና ፡ ለሀገራዊ ፡ ሥልጣን ፡ የሚውለውን ፡ የመንግሥት ፡ ኀይል ፥ በእጁ ፡ መናኛ ፡ ይዞ ፥ የግፍ ፡ መኪናው ፣ የግል ፡ መሣሪያው ፡ አድርጎ ፥ በምቀኝነት ፡ በቀል ፣ በአብሪት ፡ ሰውን ፡ በመፍጀት ፥ የመላውን ፡ ሕዝብ ፡ ሰላም ፡ እና ፡ ሰጥታ ፡ አደፍርሶ ፥ **ኢትዮጵያን** ፡ እሥልጣን ፡ ጦርነት ፡ ውስጥ ፡ ዶሏል ።

2.2 ፤ የሥልጣን ፡ ጦርነቱ ፡ ተቀጣጥሎ ፥ በግንቦት ፡ ወር ፡ 1983 ፡ ዓ.ም. ፥ **በኢ.ሕ.ዴ.ሪ.** [5] **፡ ይዘት** ፡ መፍረስ ፡ ዋዜማ ፥ የተባበሩት ፡ ያሜሪካ ፡ ኹነቶች ፡ (ዩውናይተድ ፡ ስቴይትስ ፡ ኦፍ ፡ አሜሪካ) ፡ መንግሥት ፥ **በኢ.ሕ.ዴ.ሪ ፡ ይዘት** ፡ ተወካዮች ፡ እና ፡ በተቀናቃኞቹ ፡ መኻከል ፥ በብሪታንያ ፡ መዲና ፡ ለንደን ፥ በሽምጋይነት ፡ የቀጠረው ፡ የዕርቅ ፡ ጉባኤ ፤

2.2.1 ፤ ገና ፡ ከመጀመሩ ፥ በሽምጋዩ ፡ መንግሥት ፡ ክዳት ፡ ተጨንግፏል ፤

2.2.2 ፤ ዕርቅ ፡ ሳይወርድም ፥ ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. [6] ፡ እና ፡ ሕ.ግ.ሐ.ኤ. [7] ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ገብተው ፡ አገሪቱን ፡ እንዲቄጣጠሩና ፥ የ"ሽግግር ፡ መንግሥት"ን ፡ እንዲመሠርቱ ፤ ቀጥሎም ፥ የክፍለ ፡ ሀገር ፡ ኤርትራን ፡ መኀንጠል ፡ እዳር ፡ እንዲያደርሱ ፡ ሽምጋዩ ፡ መንግሥት ፡ አላግባብ ፡ በማዘዙ ፥ የተባበሩት ፡ መንግሥታትን ፡ ሥምረት ፡ ረምርሟል ፥ ባንዲት ፡ **እግዝእት ፡ ሀገር** ፡ የውስጥ ፡ ጉዳይ ፡ ጣልቃ ፡ ገብቷል ፤ የጣልቃ ፡ ገብነት ፡ ውሳኔውንም ፡ አስፈጽሟል ፤

2.2.3 ፤ **በኢትዮጵያ** ፡ ውስጥ ፡ ሕገ ፡ ወጥነትን ፡ እና ፡ ውንብድናን ፡ አጽንቷል ፤

2.2.4 ፤ ዕርቅ ፡ ባልወረደበት ፡ ቀውጢ ፡ ኹኔታም ፥ **የሕገ ፡ መንግሥት** ፡ ማርቀቅ ፡ ኺደትን ፡ አስጀምሯል ፥ የማርቀቁንም ፡ ኺደት ፡ በመቀየስ ፥ **የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ** ፡ "ሕዝቦች" ፡

5 ኢ..ሕ.ዴ.ሪ. ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝባዊ ፡ ዴሞክራስያዊ ፡ ሪፓብሊክ ፥ (የደርግ ፡ ይዘት) ።

6 ኢ..ሕ.አ.ዴ.ግ. ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝቦች ፡ አብዮታዊ ፡ ዴሞክራስያዊ ፡ ግንባር ።

7 ሕ.ግ.ሐ.ኤ. ፤ ሕዝባዊ ፡ ግንባር ፡ ሐርነት ፡ ኤርትራ ።

በማለት ፡ ህልውናውን ፡ የካደ ፣ ፀረ ፡ **ኢትዮጵያ** ፡ የ"አፓርትሀይድ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት"ን ፡ በሀገሪቱ ፡ ላይ ፡ በእጀ ፡ መናኛ ፡ ጭኗል ፤

2.2.5 ፤ **የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ** ፡ ለዕልቂት ፣ ለጭቈና ፡ እና ፡ ለስደት ፥ ሀገሪቱንም ፡ ለብዝበዛ ፡ ዳርጓል ።

2.3 ፤ ከ 2007 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ 2010 ፡ ዓ.ም. ፡ ተጠናክሮ ፡ በቀጠለው ፡ **ሀገራዊ ፡ እግዚእናን** ፡ የማስመለስ ፡ ሕዝባዊ ፡ እንቅስቃሴ ፡ ምክንያት ፥ **የኢ.ፌ.ዴ.ሪ.** [8] ፡ **ይዘት** ፡ ለ"ሥር ፡ ነቀል" ፡ ለውጥ ፡ ዝግጁ ፡ መኾኑን ፡ አስታውቋል ፤ በተግባርም ፡ ምልክቶችን ፡ አሳይቷል ።

2.4 ፤ **የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ እግዚእና** ፡ በማክበር ፥ በሕጋዊ ፡ ሥልጣን ፡ ብቻ ፡ ሊሠራበት ፡ የሚገባውን ፡ መንግሥታዊ ፡ ኀይል ፥ የሕዝብ ፡ ይኹንታን ፡ ላገኘ ፡ ለባለዐደራ ፡ የሽግግር ፡ መንግሥት ፡ በማስረከብ ፥ ዐዲስ ፡ **ሕገ ፡ መንግሥት** ፡ ተረቆ ፡ የሚጸድቅበትን ፡ እና ፡ ዘላቂው ፡ **ሥልጡንሕዝባዊ** ፡ መንግሥት ፡ የሚቋቋምበትን ፡ ሕጋዊ ፡ አገባብ ፡ በጋራ ፡ ለማስለጥ ፡ **ኢ.ሀ.ሥ.አ.** ፡ ይተጋል ።

2.5 ፤ መሳው ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፥ በነጻ ፡ እና ፡ **ሥልጡንሕዝባዊ** ፡ ምርጫ ፡ ሠይሞ ፡ የሚያቋቁመው ፡ **ሀገራዊ ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ** ፡—

2.5.1 ፤ በተወሰነለት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፥ በሙሉ ፡ ነጻነት ፡ መክሮ ፡ እና ፡ ዘክሮ ፡ የሚያረቀውን ፡ ዐዲስ ፡ **ሕገ ፡ መንግሥት** ፡ ለሕዝብ ፡ አቅርቦ ፡ በማስጸደቅ ፥

2.5.2 ፤ በሕገ ፡ መንግሥቱም ፡ መሠረት ፡ ዐዲሱን ፡ **ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ ኹነት** ፡ (የርትዕ ፡ መንግሥት) ፡ በማቆም ፥

የሥልጣን ፡ ተገቢነትን ፡ በሀገሪቱ ፡ መልሶ ፡ ማስፈን ፡ የዚህ ፡ ሀገራዊ ፡ ሱታፌ ፡ አንድያ ፡ ዐላማ ፡ ይኾናል ።

2.6 ፤ ይህም ፡ ዐላማ ፡ እዳር ፡ እስካልደረሰ ፡ እና ፡ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ በሀገሪቱ ፡ እስካልሰፈነ ፡ ድረስ ፥ አንዳች ፡ ደኅኛም ፡ ኾነ ፡ ክፉኛ ፡ ለውጥ ፡ በሀገሪቱ ፡ ቢከታተል ፥ የሕዝብን ፡ **እግዚእና** ፡ ለዘለቄታው ፡ የማስከበሩ ፡ ሰላማዊው ፡ **የኢ.ሀ.ሥ.አ.** ፡ ትግል ፡ እስከ ፡ ሙሉ ፡ ክንዋኔው ፡ ድረስ ፡ ሳይቋረጥ ፡ ይቀጥላል ።

## አንቀጽ ፡ 3 ፤
## የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሕጋዊ ፡ ትግል ።

3.1 ፤ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፥ ያገሩን ፡ **ርትዓዊ ፡ ኹነት** ፣ የግዛቱን ፡ **ሥልጡንሕዝባዊነት** ፡ እና ፡ ነፍስ ፡ ወከፍ ፡ ነጻነቱን ፡ የሚጠብቅበትን ፡ የገዢነት ፡ መብቱን ፡ ለማስከበር ፥ በተናጠልም ፡ ኾነ ፡ በኅብረት ፥ ወይ ፡ በ**ሀገር** ፡ ደረጃ ፥ በእየጊዜው ፡ የሚፈጽማቸው ፡ የፍትሕ ፡ ክርክሮች ፥ ወይም ፡ የመሣሪያ ፡ ትግሎች ፥ የጭቈና ፡ ተቃውሞ ፡ መብቱ ፡ የሚፈቅድለት ፡ ተገቢዎች ፡ ተግባሮች ፡ ናቸው ።

3.2 ፤ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፥ ማንኛውንም ፡ ዐምባ ፡ ገነንነት ፡ ለመቃወም ፡ የሚያነሣው ፡ ጠቅላላ ፡ ትግል ፥ ያልሞት ፡ ባይ ፡ ተጋዳይነት ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፥ ነፍስ ፡ ወከፋዊ ፡ እና ፡ **ሀገራዊ ፡ እግዚእናውን** ፡ የመከላከልም ፡ የተቀደሰ ፡ መብቱ ፡ ነው ።

3.3 ፤ ለግል ፡ ጥቅም ፥ ወይም ፡ ለውጭ ፡ ኀይል ፡ መሣሪያ ፡ በመኾን ፡ **ኢትዮጵያን** ፡ ለመቈረስ ፣ ለመክፈል ፣ ለማጥፋት ፣ በከፊል ፡ ወይ ፡ በመላዋ ፡ ለባዕድ ፡ አሳልፎ ፡ ለመስጠት ፥ በነፍስ ፡ ወከፍም ፡ ኾነ ፡

8 ኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ፌዴራላዊ ፡ ዴሞክራስያዊ ፡ ሪፓብሊክ ፡ (የኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. ፡ ይዘት) ።

ባንዳች ፡ ኅብረት ፡ የሚሠራ ፡ ኹሉ ፡
**የኢትዮጵያ** ፡ ጠላት ፡ ነው ።

**አንቀጽ ፡ 4 ፤**
**ቍርጥ ፡ ሐሳብ ።**

4.1 ፤ **ኢትዮጵያን** ፥ ከወደቀባት ፡ ጥፋት ፡ አኹን ፡ የሚያድናት ፡ እና ፡ ርትዓዊ ፡ ኹነቷን ፡ መልሶ ፡ የሚሠራላት ፡ ችሎት ፥ የሕዝቧ ፡ አንድነት ፡ የሚያለማላት ፡ **ሀገራዊ ፡ እግዚእናዋ** ፡ መኾኑን ፡ ተገንዝበን ፤

4.1.1 ፤ ተወላጇ ፡ የሚመኘውን ፡ የባለቤትነት ፡ እና ፡ የነጻ ፡ ኅብረ ፡ ሰብእ ፡ ኑሮን ፡ የሚያገኘው ፥ ሕዝቧ ፥ ራሱን ፣ በራሱ ፣ ለራሱ ፡ ሲገዛ ፡ ብቻ ፡ መኾኑን ፡ ተረድተን ፤

4.1.2 ፤ እነዚህንም ፡ መሠረታውያን ፡ ጸጋዎች ፡ የሚያጐናጽፋት ፡ ችሎት ፥ የተወላጇ ፡ ባሕርያዊ ፡ ሥልጡንሕዝብና ፡ መኾኑን ፡ አምነን ፤

4.1.2.1 ፤ የሕዝቧን ፡ አንድነት ፡ በመሥራት ፥ **ሀገራዊ ፡ እግዚእናዋን** ፡ ለማልማት ፤

4.1.2.2 ፤ ሰራዊቶቿን ፡ እትእዛዟ ፡ ሥር ፡ በመመለስ ፥ የለውጡን ፡ ሰላማዊ ፡ ንቅናቄ ፡ ለማስለጥ ፤

4.1.2.3 ፤ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፥ በጠቅላላ ፡ ንቅናቄው ፡ በባሕርያዊ ፡ ባለመብትነት ፡ የሚጠይቀውን ፡ የግዛት ፡ ሥልጣን ፡ ለማስከበርና ፥ ሥልጡንሕዝብናን ፡ **በኢትዮጵያ** ፡ መልሶ ፡ ለማስፈን ፥ ቅዱስ ፡ ለገቻ ፡ ገብተናል ፤ ለገቻችንንም ፡ እፍጻሜ ፡ ሳናደርስ ፡ ላናርፍ ፥ ላንመለስ ፡ ቈርጠናል ።

4.2 ፤ ቍርጥ ፡ ሐሳባችንን ፡ እመልካም ፡ ፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፦

***"የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት — ኢ.ሀ.ሥ.አ."***

በተሠኘ ፡ መጠሪያ ፥ አንድነታዊ ፡ አካላችንን ፡ አቁመን ፥ ግብሩን ፡ ያከናውንልን ፡ ዘንድ ፥ ***ባምስተኛው ፡ አንቀጽ*** ፡ የተመለከተውን ፡ **ፈጻሚ ፡ ምክር** ፡ ሠርተን ፥ ሕዝባዊ ፡ ሥልጣናችንን ፡ ሠይመነዋል ።

**አንቀጽ ፡ 5 ፤**
**የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ።**

5.1 ፤ **የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት** ፥ በ***አንቀጽ ፡ 4*** ፡ የተመለከተውን ፡ ቍርጥ ፡ ሐሳባችንን ፡ በገቢር ፡ ያከናውንልን ፡ ዘንድ ፥ አንድ ፡ ሀገራዊ ፡ **ፈጻሚ ፡ ምክር** ፡ ይኖረዋል ።

5.2 ፤ ፈጻሚ ፡ ምክሩ ፦

አንድ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፤

አንድ ፡ ምክትል ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፤

ሦስት ፡ አባሎች ፤

አንድ ፡ በኸሮንድ ፤

አንድ ፡ ጠቅላይ ፡ ጸሓፊ ፤

በድምሩ ፡ ሰባት ፡ በስም ፡ የመረጥንለት ፡ መማክርት ፡ ይኖሩታል ።

5.3 ፤ በየኀላፊነቱ ፡ የሚያስቀምጣቸውን ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ፈጻሚ ፡ ምክሩ ፡ ይሠይማል ።

5.4 ፤ ፈጻሚ ፡ ምክሩ ፡ ሥራውን ፡ የሚያከናውንበት ፡ አንድ ፡ ሀገራዊ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡

ይኖረዋል ።  መንበሩን ፡ እተመቸው ፡ ቦታ ፡ የማድረጉ ፡ ምርጫ ፡ የርሱ ፡ ነው ።

5.5 ፤ ፈጻሚ ፡ ምክሩ ፡ የውስጥ ፡ ደንቡን ፣ የዘርፍ ፡ ጉባኤዎቹን ፣ የክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶቹን ፡ ደረጃ ፡ እና ፡ ብዛት ፣ የሠራተኞቹን ፡ ዐይነት ፡ እና ፡ መጠን ፣ የሥራ ፡ ማስኬጃውን ፡ ራሱ ፡ ይወስናል ።

## አንቀጽ ፡ 6 ፤
## የኢ.ህ.ሥ.አ. ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፡ ግብር ።

6.1 ፤ **የውንብድና ፡ ይዘትን** ፡ ከ**ኢትዮጵያ** ፡ አስወግዶ ፡ **የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ እግዚእና** ፡ መልሶ ፡ ማስከበር ፤

6.2 ፤ **እግዚእናውን** ፡ ተረክቦ ፡ ከለበሰበት ፥ ማለት ፥ **የውንብድና ፡ ይዘት** ፡ ከተወገደበት ፡ ዕለት ፡ አንሥቶ ፥ ከስድስት ፡ ወር ፡ በማያልፍ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፥ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ** ፡ ሀገራዊ ፡ ኹነቱን ፡ በውዴታው ፡ እንዲከውን ፥ ባልተጨቈነ ፡ ኅሊናው ፥ ባልተጨነቀ ፡ ልቦናው ፡ እና ፡ ባልተገደደ ፡ ፈቃዱ ፡ ዐዲስ ፡ **ክዋኔን** ፡ ወይም ፡ **ሕገ ፡ መንግሥትን** ፡ የሚሠራለትን ፡ **ሀገራዊ ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤውን** ፡ በሙሉ ፡ ነጻነት ፡ እና ፡ በብሔራዊ ፡ መረጣ [9] ፡ ለማቋቋም ፡ የሚያሻውን ፡ ሰጥታ ፡ እና ፡ ምቹት ፡ ማረጋገጥ ፤ የሚፈለገውንም ፡ ሙሉ ፡ አገልግሎት ፡ ማበርከት ፤

6.3 ፤ **ሀገራዊው ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ** ፡ ዐዲሱን ፡ **ክዋኔ** ፡ ከወሰነበት ፡ ዕለት ፡ አንሥቶ ፥ መንፈቅ ፡ በማያልፍ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፥ በዚሁ ፡ **ክዋኔ** ፡ መሠረት ፥ ግዛቱን ፡ በሙሉ ፡ ነጻነት ፡ የሚያቋቁምበትን ፡ ምቹት ፡ ማረጋገጥ ፤

6.4 ፤ ዐዲሱ ፡ ግዛት ፡ እስከሚቋቋምበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፥ ታሪካዊውን ፡ የሀገሪቱን ፡ ሥርዐተ ፡ መንግሥት ፡ (ወይም ፡ ዐፄ ፡ ሥር) ፡ ፍልስፍናን ፡ ጠንቅቆ ፡ በማወቅ ፡ እና ፡ በማክበር ፣ አሠራሩንም ፡ በማዘመን ፥ አስቀድሞ ፡ በዝርዝር ፡ በተደነገገለት ፡ መመሪያ ፡ መሠረት ፥ የሀገሪቱን ፡ ጠቅላላ ፡ አስተዳደር ፡ ማከናወን ፤

6.5 ፤ ያዲሱ ፡ ግዛት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የሥራ ፡ መንበራቸውን ፡ በወግ ፡ በተረከቡበት ፡ ዕለት ፥ ፈጻሚ ፡ ምክሩ ፡ ሥራውን ፡ ፈጽሞ ፣ ስፍራውን ፡ ለቆ ፡ መበተን ፡ ይኾናል ።

## አንቀጽ ፡ 7 ፤
## የኢ.ህ.ሥ.አ. ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፡ ኀላፊነት ፣ መብት ፣ ሥልጣንና ፡ ዕድሜ ።

7.1 ፤ **የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር** ፥ በ**ኢትዮጵያ ፡ መንግሥት** ፡ መብት ፥ ኀላፊነት ፡ እና ፡ ሥልጣን ፡ ይሠራል ።

7.2 ፤ **የኢ.ህ.ሥ.አ. ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር** ፡ የሥልጣን ፡ ዕድሜ ፥ በዚህ ፡ ጠቅላላ ፡ ውሳኔ ፡ የተነገረውን ፡ መልእክቱን ፡ በገቢር ፡ ከዠመረበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፥ በንኡስ ፡ ***አንቀጽ ፡ 6.5*** ፡ የተወሰነው ፡ እሚፈጸምበት ፡ ዕለት ፡ የሚደርስ ፥ ከዚያ ፡ በፊት ፡ የማይመለስ ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የማይታደስ ፡ ነው ፨

| ሙሉ ፡ ስም | ዘንዳ | ሞያ |
|---|---|---|
| _ _ _ _ _ _ _ | _ _ _ _ _ _ _ | _ _ _ _ _ _ _ |

9 <u>ብሔራዊ ፡ መረጣ</u> ፤ እመምረጥ ፡ ዕድሜ ፡ የደረሱ ፡ እና ፡ ሕጋዊ ፡ እገዳ ፡ ያልተጣለባቸው ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ኹሉ ፥ ምንም ፡ ዐይነት ፡ የጾታ ፡ የሃይማኖት ፡ የሀብት ፡ የሌላም ፡ ልዩነት ፡ ሳይደረግባቸው ፥ የምርጫ ፡ ድምፃቸውን ፡ የሚሰጡበት ፡ ብሔራዊ ፡ ምርጫ ፡ (universal suffrage) ።

ተቀጥሎ - 2 ፤

# ዐጪር ፡

# የቃላት ፡ መፍቻ ።

ኢ ሀ ሥ አ

| ዐጪር ፡ ግስ (ዐማርኛ/ግእዝ) | ፍቾ | short glossary (English) |
|---|---|---|
| | | |
| ሀገራዊ ፡ (ስም) | ባለቤት ፣ ባላገር ፡ (በዓለ ፡ ሀገር) ፣ ዐማራዊ ፣ ዐምሐራዊ | citizen |
| ሀገራዊ ፡ (ቅጽል) | የሀገር | citizen *(adj.)*, national *(adj.)* |
| ሀገራዊ ፡ ሒሳብ | | national accounts |
| ሀገራዊ ፡ ሒሳብ ፡ አያያዝ | | national accounting |
| ሀገራዊ ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ | የሀገርን ፡ ክዋኔ ፡ ወይም ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የሚሠራ ፡ የሕዝብ ፡ ተወካዮች ፡ ምክር ፡ ቤት ። | citizen/national constituent assembly |
| ሀገራዊ ፡ ኪዳን | ሀገራዊ ፡ ውል | citizen contract, social contract |
| ሀገራዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር | | national executive council |
| ልማት | ብጀታ ፣ እድገት | development |
| ልቅም | የአኃዝም ፡ ኾነ ፡ የማንኛውም ፡ መረጃ ፡ ልቅም ፥ አላድ | data |
| ልዕልና | የበላይነት | supremacy |
| ሐራ | ነጻ ፥ በራስ ፡ ዐደር | independent / free |
| ሐጋጊ | ሕግን ፡ አውጪ | legislative |
| ሐጋጊ ፡ ሥልጣን | ሕግን ፡ አውጪ ፡ ሥልጣን | legislative power |
| ሕዝባዊ ፡ ፈረዳ | ውሳኔ-ሕዝብ ፣ ፈረዳ | referendum |
| መረብ | | network |
| መርሐ ፡ ሰሜን | | compass |
| መርበቢያ | የመርበብት ፡ መገኛ | web site |
| መርበብት | "ኢንተርኔት" | internet |
| መሳሊያ | መግበር | software |
| መባሕታዊ | | diplomatic |
| መባሕት | | diplomat |
| መብዕል | ብዕል ፣ መጥሪት | capital |
| መነሻ | | starting point |
| መነሻ | | paragraph |
| መከየድ | ማረማመጃ | platform |
| መዜንው | "ጋዜጣ" | journal |
| መዜንው | ዜና ፡ ማሠራጫ | news media |
| መዜንው | ዜነኛ ፥ የዜና ፡ ሰው | journalist |
| መደብ | መነሻ | base |
| መደብ-ዓመት | መነሻ ፡ ዓመት | base year |
| መጋቢ | "ሚኒስትር" | minister |
| መግበር | መሣሪያ | tool |
| መጥሪ/መጥሪት | ጠራዒ/ት | economic agent |
| መጥሪት | መብዕል | capital |
| ማሚሸሻ | | deflator |
| ማስሊያ | የስሌት ፡ መኪና | computer |
| ማወራኛ | መልፈፊያ ፣ ማገናኛ | media |
| ምልከኛ | | imperialist |
| ምልክዮሽ | | imperialism |
| ምሕቃፍ | ማቀፊያ | framework |
| ምሕዋር | መንገድ ፣ መኬጃ | circuit |
| ምኅዳራዊ | አካባቢያዊ | ecological |
| ምኅዳር | አካባቢ | ecosystem |
| ምንሃባዊ ፡ ወጀድ | የምንሃብ ፡ ድርጅቶች ፡ ሰፈር | industrial park |
| ምንሃብ | የመሥሪያ ፡ ቦታው ፡ እና ፡ ሥርዐቱ ፥ "ፋብሪቃ" | industry |
| ምእትያ | ምእት ፡ ዓመት | century |
| ምድራስ | "ዩኒቨርስቲ" | university |
| ምድራግ | ተልእኮ | commission |
| ምድራግ | | agency |
| ምጋቤ | "ሚኒስቴር" | ministry |
| ምጥራይ | የጥርየት ፡ ሥርዐት | economic system, macro-economy |
| ሚሸሻ | የዋጋ ፡ ሚሸሻ | deflation |
| ሥሉጥ | ሥልጡን | civil, civic |
| ሥሉጥ ፡ ማኅበር | ሥልጡን ፡ ማኅበር | civil society |
| ሥልጡን | ሥሉጥ | democrat |
| ሥልጡንሕዝባዊ | የሥልጡን ፡ ሕዝብ | democratic |
| ሥልጡንሕዝብና | ሥልጡንሕዝብነት | democracy |

| ዐጪር ፡ ግስ (ዐማርኛ/ግእዝ) | ፎቻ | short glossary (English) |
|---|---|---|
| ሥልጣን | መብት ፣ እግዚእና ፣ ኀላፊነት | authority |
| ሥልጣን ፡ ክፈላ | አንድ ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጣን ፡ በሕጋጊ ፣ በፈጻሚ ፡ እና ፡ በፈታሒ ፡ ሥልጣናት ፡ ሲከፈል | separation of power |
| ሥምረት | ስምምነት | convention |
| ሥርዐተ ፡ ፀሓይ | ፀሓይ ፡ እና ፡ ዘጠኙ ፡ ተንቀባቢዎች ፡ አንድ'ጋ | solar system |
| ርትዓዊ ፡ ኹነት | የርትዕ ፡ መንግሥት ፣ የርትዕ ፡ ኹነት | State of Right |
| ስሕበት | ስበት | gravity |
| ስያሰኛ | የነገረ ፡ ስያሳ ፡ አጥኚ | political scientist |
| ስያሰኛ | የስያሳ ፡ ሰው ፣ "ፖለቲከኛ" | politician |
| ስያሳ | ሥነ ፡ ግዛት ፥ "ፖለቲካ" | politics |
| ስያሳዊ | የስያስ ፡ ወይም ፡ የስያሳ | political *(adj.)* |
| ስያስ | ዘዴ | policy |
| ስያስኛ | ነገረ ፡ ስያሳ | political science |
| ሽልግ | ግምት | estimate |
| ሽቦ–አልቦ | ነፋስ ፡ ስልክ ፥ አለሽቦ ፡ የሚተላለፍ ፡ መልክት | wireless |
| ቀረባ | አቀራረብ ፥ ስልት | approach |
| ቅያስ | መመሪያ | road map |
| በሐረ | መደረ ፥ ሰፋ ፥ ተንጣለለ ። | expand |
| በቀርታ | | exception |
| ብሔራዊ | የምድር | territorial |
| ብሔራዊ | ዓለም ፡ ዐቀፍ | universal |
| ብሔራዊ ፡ መረጣ | የጾታ ፣ የኑሮ ፡ ደረጃ ፣ ወዘተርፈ ፡ ... ፡ ልዩነት ፡ የማይደረግበት ፡ ምርጫ | universal suffrage |
| ብሔር | ምድር ፡ (ሲወሰን)/ ስፋት ፣ ዓለም | territory / universe |
| ብቸ ፡ ሥሉጥ | ብቸ ፡ ገኘ | autocrat |
| ብውሕና | | diplomacy |
| ተቋም | | institute, institution |
| ተንቀባቢ | እንደ ፡ ምድር ፡ በፀሓይ ፡ ዙሪያ ፡ የሚንዣበብ ። | planet |
| ተዳባይ | | con-federal |
| ተዳብሎ | | confederation |
| ተገቢነት | ሕጋዊነት | legitimacy |
| ትልም | ኸርማሬ | initiative |
| ትውፊት | ልማድ ፥ ባህል | tradition |
| ቹምቹማት | ቹፍግነት | density |
| ኀይል | | power |
| ኀይል | | might |
| ኀይል | ጉልበት | force/energy |
| ኀሊ | | idea |
| ኅዋ | ጠፈር | space |
| ነኰርኳር | መገለባበጥ ፥ መለዋወጥ ፤ የሥርዐት ፡ ለውጥ ። | revolution |
| የነዋሪዎች ፡ ፍድፋዴ | ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ የነዋሪዎች ፡ መባዛት | population explosion |
| ነጂ–አልቦ | ገዛውን ፡ የሚንቀሳቀስ | driver-less |
| ነጠላ–ጥርየት | ጥርየት | micro-economy |
| ንረት | የዋጋ ፡ ንረት | inflation |
| ንዛኸ | ጋዝ ፣ የእንፋሎት ፡ ዐይነት | gas |
| አህጉራት | (ብዙ) ፡ ሀገሮች | (many) countries |
| አህጉራዊ | ወሰ–አህጉራዊ በይነ–አህጉራዊ የሀገሮች ፡ የጋራ | international |
| አህጉራዊ ፡ የገንዘብ ፡ ቋት ፡ (አ.ገ.ቋ.) | የዓለም ፡ ባንክ ፡ ዘርፍ ፡ ድርጅት | International Monetary Fund (I.M.F.) |
| አህጉር | (ኹለት) ፡ ሀገሮች | (two) countries |
| አላድ | ልቅም | data |
| አምሳያ | ምስያ | synonym |
| አስኳል | ውስጣውስጥ | core |
| አንከርት ፡ ስልክ | የኪስ ፡ ስልክ | mobile phone |
| አንድያ | አንድ ፡ ብቻ | unique, sole |
| አካባቢ | | environment |
| አወነ | እውን ፡ አደረገ | realise, achieve |
| አገዛዝ | ግዛት | government |
| የኢትዮጵያ ፡ ብሔር | የኢትዮጵያ ፡ ምድር | Ethiopian territory |
| ኢትዮጵያዊ | የኢትዮጵያ ፡ ተወላጅ | Ethiopian |

| ዐጪር ፡ ግስ (ዐማርኛ/ግእዝ) | ፍቾ | short glossary (English) |
|---|---|---|
| ኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊ | በኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊነት ፡ የሚገኝ | Ethiopian citizen |
| እንሻ | ማነስ ፥ መዶግዶግ | decrease |
| እውነት | እውንነት | reality |
| እውን | | real, fact |
| እግዚእ | ገዢ | sovereign |
| እግዚእና | ገዢነት | sovereignty |
| ከወነ | ሠራ | constitute |
| ከዋኝ | | constituent |
| ከዋኝ ፡ ምክር | ከዋኝ ፡ ጉባኤ | constituent assembly |
| ከዋኝ ፡ ጉባኤ | ከዋኝ ፡ ምክር | constituent assembly |
| ኪ..ማ. | ኪሎሜትር ፡ ማእዘን ፥ ኪሎሜትር ፡ መረባ | $km^2$ |
| ኪነት | | technology |
| ኪን | | technique |
| ኪዳን | ውል ፣ ሥምረት | contract, charter |
| ካልኢት | የጊዜ ፡ መለኪያ ፤ 60 ፡ ካልኢት ፡ 1 ፡ ደቂቃ ፡ ይኾናል | second |
| ክሂል | | potential |
| ክሂሎት | ችሎት | potentiality |
| ክዋኒት | ሐውልት | obelisk |
| ክዋኔ | ሕገ ፡ መንግሥት | constitution |
| ክፍለ ፡ ጥርየት | የጥርየት ፡ ቀጣና | economic sector |
| ክፍለት | አከፋፈል ፣ አለያየት | partition |
| ኹለትዮ ፡ ንምራ | የኹለት ፡ ቤት ፡ አኃዝ ፡ (0 ፣ 1) | binary digit |
| ኹነት / ኩነት | መንግሥት ፥ የተከወነ ፣ ክዋኔ ፡ ያለው | State |
| ወጀብ | ዐውሎ ፡ ነፋስን ፡ እና ፡ ኀይለኛ ፡ ዝናብን ፡ የቀላቀለ ፥ አውዳሚ ፡ የአየር ፡ ጠባይ ። | hurricane |
| ወጀድ | ዐጸድ ፣ ግቢ | park |
| ወገብጌ | | equator |
| ወገዳ | የማስወገድ ፡ ድርጊት | purge |
| ውልደት | ትውልድ | nation |
| ውርኝት | ለፈፋ | broadcast |
| ዐማራ | ዐም ፡ ሐራ ፥ ነጻ ፡ ሕዝብ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ | Amhara, Ethiopian citizenry |
| ዐማራዊ | ሀገራዊ ፥ ዐምሐራዊ | citizen |
| ዐምሐራዊ | ዐማራዊ | citizen |
| ዑደት | ዙር | orbit |
| ዜነኛ | "ጋዜጠኛ" | journalist |
| ዞግ ፡ (ዘውግ) | የጎሳ ፡ ክፍል | clan |
| የሀገር ፡ ውስጥ ፡ ጠቅላላ ፡ ምርት ፡ (ሀ.ው.ጠ.ም.) | | gross domestic product (G.D.P.) |
| የሀገር ፡ ውስጥ ፡ ጠቅላላ ፡ ምርት ፡ በነፍስ-ወከፍ | | gross domestic product (G.D.P.) per capita |
| የሥልጣን ፡ ተገቢነት | የሥልጣን ፡ ሕጋዊነት | legitimacy of power |
| የርትዕ ፡ ኹነት | ርትዓዊ ፡ ኹነት | State of Right |
| የባሕር ፡ ብሔር | ባሕራዊ ፡ ብሔር ፣ የባሕር ፡ ግዛት | territorial waters |
| የችርቻሮ ፡ ዋጋ ፡ ቋም | የገበያ ፡ ዋጋ ፡ መጠቌሚያ | retail price index |
| የአንከርት ፡ ስልክ ፡ ኪነት | | mobile phone technology |
| የአየር ፡ ብሔር | የአየር ፡ ግዛት | aerial territory |
| የየብስ ፡ ብሔር | ምድራዊ ፡ ወይም ፡ የብሳዊ ፡ ግዛት | continental territory |
| ይዘት | ይዘታ | dictatorial régime |
| ደረጃ | ዕርከን | degree |
| ድርገት | ደርግ | committee |
| ደርግ | አንድነት ፣ ጉባኤ ፣ ድርገት | committee |
| ደባይ | በደባልነት ፡ የሚያሳድር | federal |
| ደፈር | የተራራ ፡ ጫፍ | highest point, summit |
| ድርስ | ክንዋኔ | event |
| ድቦላ | ድባሌ ፥ ደባል ፡ አድርጎ ፡ የሚይዝ ፡ ሥርዐት | federation |
| ድባሌ ፡ (ድባሌ) | ድቦላ ፥ ደባል ፡ አድርጎ ፡ የሚይዝ ፡ ሥርዐት | federation |

| ዐጨር ፡ ግስ (ዐማርኛ/ግእዝ) | ፍቺ | short glossary (English) |
|---|---|---|
| ጅምላ-ጥርየት | ምጥራይ | macro-economy |
| ጋዝ | ንዛዥ | gas |
| ግለኛ | ባለግል ፥ ሰው | individual (n.) |
| ግል | | private |
| ግንኙት | ግንኙነት | connection |
| ግዑዝ | ያልወገነ ፥ ገለልተኛ | neutral |
| ግዑዝነት | አለመወገን | neutrality |
| ግዛት | አገዛዝ | government |
| ግጽው | ሥዕል ፥ ግጻዌ | figure, image |
| ግጽው | ልቅም | figure, statistics |
| ጎሳ | ነገድ | tribe |
| ጉልበት | ኀይል | energy |
| ጠቅላይ ፡ መጋቢ | ጠቅላይ ፡ "ሚኒስትር" | prime minister |
| ጠረየ | | economize |
| ጥሪት | ሀብት | wealth |
| ጥርየተኛ | የጥርየትኛ ፡ ባለሚያ | economist |
| ጥርየት | የሀብት ፡ ፈጠራ ፣ ግብይት ፣ ፍጆታ ፡ እና ፡ አስተዳደር ፡ ሥርዐት | economy |
| ጥርየትኛ | ሥነ ፡ ጥርየት ፥ የጥርየት ፡ ጥናት | economics |
| ፈረዳ | ውሳኔ-ሕዝብ ፣ ሕዝባዊ ፡ ፈረዳ | referendum |
| ፈታሒ | ፈራጅ | judicial |
| ፈታሒ ፡ ሥልጣን | የፍርድ ፡ ሥልጣን | judiciary |
| ፈጻሚ | አድራጊ | executive |
| ፈጻሚ ፡ ሥልጣን | የአስተዳደር ፡ ሥልጣን | executive power |
| ፈጻሚ ፡ ምክር | ፈጻሚ ፡ ጉባኤ | executive council |
| ፍልቅ | የፈለቀ | |
| ፍልቅ | ሥንጥቅ | rift |
| ፍልቅ ፡ ሸለቆ | ሥንጥቅ ፡ ሸለቆ | Rift Valley |

# ተቀጥ፟ላ፟ – 3 ፫

# የሀገራዊ ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ ፡ አባላት ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የውከላ ፡ ኺደት ፥ በሥዕላዊ ፡ መክሠቻ ።

―――

# የሀገራዊ ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ ፡ አባላት ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የውከላ ፡ ኺደት ፣ በሥዕላዊ ፡ መክሠቻ ።

ከቀበሌ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ መሳ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሚከናወነው ፡ **የሀገራዊ ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ** ፡ አባላት ፡ **የውከላ** ፡ ኺደት ፡ ሦስት ፡ ዕርከኖች ፡ ይኖሩታል ፡—

1 ኛ ፡ ዕርከን ፤ **የቀበሌ** ፡ ውከላ ፤

2 ኛ ፡ ዕርከን ፤ **የወረዳ** ፡ ውከላ ፤

3 ኛ ፡ ዕርከን ፤ **የሀገር** ፡ ውከላ ።

ኺደቱ ፡ በጠቅላላ ፡ አገላለጽ ፡ በዋናው ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ ተገልጿል ። እዚህ ፡ ላይ ፡ የምንሞክረው ፣ ኺደቱን ፡ በቀላሉ ፡ ለመገንዘብ ፡ እንዲቻል ፣ በሥዕላዊ ፡ መክሠቻ ፡ በመታገዝ ፣ በተለይ ፡ ባንድ ፡ ወረዳ ፡ ላይ ፡ አተኲረን ፣ የኺደቱን ፡ ረድፎች ፡ ለማሳየት ፡ ይኾናል ።


የምናተኲረው ፡ በ**ወሎ ፡ ክፍለ ፡ ሀገር** ፣ ጥንታዊው ፡ የላሊበላ ፡ ከተማ ፡ በሚገኝበት ፡ በ**ቡግና** ፡ ወረዳ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ። *(ቢጋር ፡ 1)*

ቡግና ፡ ወረዳ ፡ 45 ፡ ቀበሌዎች ፡ አሉት ፡ *(ቢጋር ፡ 2)* ። የነዋሪዎቿ ፡ ብዛት ፡ 228'000 ፡ ይገመተታል [10] ። አኃዙ ፡ ***"1 ፡ ተወካይ ፡ ለ 200'000 ፡ ነዋሪ"*** ፡ የሚለውን ፡ መስፈሪያ ፡ ስለሚያሟላ ፣ ቡግና ፡ ወረዳ ፡ አንድ ፡ ተወካይ ፡ **ለሀገራዊው ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ** ፡ መርጦ ፡ መላክ ፡ ይችላል ።


በምርጫው ፡ የመዠመሪያ ፡ ዕርከን ፣ ማለት ፣ በቀበሌ ፡ ደረጃ ፣ 45 ቱም ፡ የቡግና ፡ ወረዳ ፡ ቀበሌዎች ፣ ለመመረጥ ፡ ብቃት ፡ ካላቸው ፡ ነዋሪዎቻቸው ፡ ውስጥ ፣ በቀበሌ ፡ ሦስት ፡ ተወካዮችን ፣ በድምሩ ፡ 135 ፡ የቀበሌ ፡ ተወካዮችን ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ መርጠው ፡ ለቡግና ፡ ወረዳ ፡ የተወካዮች ፡ ጉባኤ ፡ ይልካሉ ። *(ቢጋር ፡ 3)*

በምርጫው ፡ 2 ኛ ፡ ዕርከን ፣ እነዚህ ፡ 135 ፡ የቀበሌ ፡ ተወካዮች ፡ ተሰብስበው ፣ **የወረዳውን ፡ ምክር ፡ ቤት** ፡ ይመሠርታሉ ።

በምርጫው ፡ 3 ኛ ፡ ዕርከን ፣ **የወረዳው ፡ ምክር ፡ ቤት** ፡ ከመኻከሉ ፡ ሦስት ፡ የወረዳ ፡ ተወካዮችን ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ መርጦ ፣ አብላጫ ፡ ድምፅ ፡ ያገኘውን ፡ ተወካይ ፡ **በቡግና ፡ ወረዳ ፡ ሕዝብ ፡ እንደራሴነት** ፡ **ለሀገራዊው ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ** ፡ ይልካል ፤ የቀሩትን ፡ ኹለት ፡ ተመራጮች ፡ በተጠባባቂነት ፡ መዝግቦ ፣ የወረዳው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ **ሊቀ ፡ መንበር** ፡ እና ፡ **ምክትል ፡ ሊቀ ፡ መንበር** ፡ ብሎ ፡ ይሾማቸዋል ።




*(ቢጋር ፡ 1) ቡግና ፡ ወረዳ ፡ በወሎ ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ።*




*(ቢጋር ፡ 2) የቡግና ፡ ወረዳ ፡ 45 ፡ ቀበሌዎች ።*

የቡግና ፡ **ወረዳ ፡ ሕዝብ ፡ እንደራሴ** ፣ ከ 64 ቱ ፡ የወሎ ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ የሕዝብ ፡ እንደራሴዎችና ፡ ከ 611 ዱ ፡ የመሳ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሕዝብ ፡ እንደራሴዎች ፡ ጋራ ፣ **የሀገራዊ ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ** ፡ መቀመጫውን ፡ በወግ ፡ ይይዛል ። *(ቢጋር ፡ 3)*

10 የኢ..ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ማእከላዊ ፡ የአኃዝ ፡ ምድራግ ፣ በ 1986 ፡ ዓ.ም. ፡ አካኼድኩ ፡ ባለው ፡ የነዋሪዎች ፡ ቈጠራ ፣ ለቡግና ፡ ወረዳ ፡ 171,333 ፡ ነዋሪዎች ፡ መዝግቦ ፡ ነበር ። ካ 13 ፡ ዓመታት ፡ በኋላ ፡ በ 1998 ፡ ዓ.ም. ፡ ባካኼደው ፡ ቈጠራው ፡ ግን ፣ አኃዙን ፡ ግማሽ ፡ በግማሽ ፡ በመቀነስ ፡ 75,486 ፡ ብቻ ፡ መቍጠሩን ፡ በዘገባው ፡ አስታውቆናል ። በኹለቱ ፡ ቈጠራዎች ፡ መኻከል ፡ ታሪክ ፡ የመዘገበው ፡ አንዳች ፡ የሕዝብ ፡ ፍልሰት ፡ ወይ ፡ ዕልቂት ፡ ስለሌለ ፣ የተለመደው ፡ የአኃዝ ፡ ማጭበርበር ፡ መፈጸሙን ፡ ያመለክታል ።

ኢ ሀ ሥ አ




*(ቢ.ጋር ፡ 3) የሀገራዊው ፡ ከዋኙ ፡ ጉባኤ ፡ 611 ፡ መቀመጫዎች ፡ ክፍለ ፡ ሀገራዊ ፡ ምጣኔ ።*

# ተቀጥላ - 4 ፤

## የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ወቅት ፥
## የሀገራዊ ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ ፡ አባላት ፡ ምጣኔ ፥
## በክፍላተ ፡ ሀገሩ ፡ ነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ መሠረት ።

# የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ወቅት ፥ የሀገራዊ ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ ፡ አባላት ፡ ምጣኔ ፥ በክፍላተ ፡ ሀገሩ ፡ ነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ መሠረት ።

የእያንዳንዱን ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ የነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ በተመለከተ ፥ ከደርግ ፡ ዘመን ፡ አንሥቶ ፥ ባለፉት ፡ 50 ፡ ዓመታት ፡ በኢትዮጵያ ፡ **ማእከላዊ ፡ የአኃዝ ፡ ምድራግ** ፡ (Central Statistical Agency) ፡ የተሰናዱት ፡ አኃዞች ፥ **በኢትዮጵያ** ፡ የ"አፓርትሀይድ" ፡ ሥርዐትን ፡ ለመትከል ፡ እንዲያመቹ ፥ በእየጊዜው ፡ የተነካኩ ፡ እና ፡ የተበጃጁ ፡ በመኾናቸው ፡ ይህ ፡ ጥናት ፡ አስወግዷቸዋል ። በምትካቸው ፥ ከምንም ፡ ዐይነት ፡ ፀረ-ሀገር ፡ ዐላማ ፡ በጸዳ ፡ መንፈስ ፥ በ 1938 ፡ ዓ.ም. (+) ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ መንግሥት ፡ በሀገር ፡ ግዛት ፡ ምጋቤ ፡ የተካኼደውን ፡ ሀገራዊ ፡ የነዋሪዎች ፡ ቈጠራ ፡ መነሻ ፡ አድርጓል ።

ባለፉት ፡ 77 ፡ ዓመታት ፡ በታዩት ፡ የነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ እድገት ፡ ረገድ ፥ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ምንጮች ፡ የተገኙትንም ፡ መረጃዎች ፡ በማጠናቀር ፥ ለ 2015 ፡ ዓ.ም. ፥ በእየክፍለ ፡ ሀገሮቹ ፡ አንጻር ፡ የተገመቱትን ፡ አኃዞች ፡ በሰንጠረዥ ፡ መልክ ፡ እንደሚከተለው ፡ አቅርበናል ። *(የጥናቱን ፡ ሙሉ ፡ ዝርዝር ፡ ከ"ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፡ ማግኘት ፡ ይቻላል ። )*

ማንኛውንም ፡ አስተያየት ፣ ዕርማት ፣ ምክር ፣ ወዘተርፈ ፡ ሊለግሱን ፡ የሚሹ ፡ ኹሉ ፥ በእ-ጦማር ፡ አድራሻችን ፡ በ ፦


sh1@ttomar.net

ሊያደርሱልን ፡ እንደሚችሉ ፡ ባክብሮት ፡ እናስታውቃለን ።

**የሀገራዊ ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ ፡ አባላት ፡ ክፍለ ፡ ሀገራዊ ፡ ምጣኔ ፤**

| ክፍለ ፡ ሀገር | የነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ በ 2015 ፡ ዓ.ም. | | የተወካዮች ፡ ብዛት ፡ (1 ፡ ተወካይ ፡ ለ 200'000 ፡ ነዋሪዎች) | |
|---|---|---|---|---|
| | (በሚልዮን) | (በ%) | | (ድማሪ) |
| ሸዋ | 16.7 | 13.8 % | 84 | (84) |
| ጐዣም | 13.4 | 11.0 % | 67 | (151) |
| ወሎ | 12.8 | 10.5 % | 64 | (215) |
| ጐንደር | 12.2 | 10.0 % | 61 | (276) |
| መናገሻ | 8.5 | 7.0 % | 43 | (319) |
| ሲዳሞ | 8.3 | 6.8 % | 42 | (361) |
| ትግራይ | 7.8 | 6.4 % | 39 | (400) |
| ሐረርጌ | 7.2 | 5.9 % | 36 | (436) |
| ጋሞ ፡ ጎፋ | 6.7 | 5.5 % | 34 | (470) |
| ከፋ | 6.7 | 5.5 % | 34 | (504) |
| ዐሩሲ | 5.6 | 4.6 % | 28 | (532) |
| ወለጋ | 4.5 | 3.7 % | 23 | (555) |
| ኢሉባቦር | 3.9 | 3.2 % | 20 | (575) |
| ባሌ | 3.9 | 3.2 % | 20 | (595) |
| ኤርትራ | 3.2 | 2.6 % | 16 | (611) |
| ኢትዮጵያ | 121.4 | 100.00% | 611 | |

(+) ኤርትራን ፡ እና ፡ የኦጋዴን ፡ አውራጃን ፡ ሳይጨምር ፥ በቀሩት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክፍሎች ፡ በ 1938 ፡ ዓ.ም. ፡ በተደረገው ፡ የነዋሪዎች ፡ ቈጠራ ፡ መሠረት ፥ የተገኘው ፡ ግምት ፡ 30 ፡ ሚልዮን ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፥ ካ 12 ፡ ዓመታት ፡ በኋላ ፥ በ 1950 ፡ ዓ.ም. ፥ ለተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ የተላለፈው ፡ አኃዝ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ትእዛዝ ፡ በ 8 ፡ ሚልዮን ፡ ተቀንሶ ፥ 22 ፡ ሚልዮን ፡ ተብሎ ፡ ነበር ። ይህን ፡ ለመወሰን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ምን ፡ እንዳስገደዳቸው ፡ በትኽክል ፡ ባይታወቅም ፥ በወቅቱ ፡ የተሰጠው ፡ ምክንያት ፦ *ኢትዮጵያ ፡ ለተ.መ.ድ. ፡ በእየዓመቱ ፡ የምታገባው ፡ መዋጮ ፡ በነዋሪዎቿ ፡ መጠን ፡ ስለሚሰላ ፥ የመዋጮውን ፡ መጠን ፡ ለመቀነስ ፡ ታስቦ ፡ ነው ፡ የሚል* ፡ ነበር ። የኾነው ፡ ኾኖ ፥ ይህ ፡ ዝቅተኛ ፡ መነሻ ፥ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ "ፍድፋዴ" ፡ መግታትን ፡ ለሚሹ ፡ የውጭ ፡ ኀይሎች ፥ በእየጊዜው ፡ የሚመነደግ ፡ አኃዝን ፡ በመልቀቅ ፥ የወሊድ ፡ መቈጣጠሪያ ፡ ሥራዎችን ፡ በሰፊው ፡ ለማስፈጸም ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ኾኗቸዋል ። በመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ወቅት ፥ ከዋነኛዎቹ ፡ ሥራዎች ፡ አንዱ ፥ የኢትዮጵያን ፡ **ማእከላዊ ፡ የአኃዝ ፡ ምድራግ** ፡ *(Central Statistical Agency)* ፡ ሥራ ፡ ማስመርመር ፡ ይኾናል ።




## የነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ በኪሎ-ሜትር ፡ ማእዘን ፤





**መናገሻ ፡ አውራጃ** ፤ 941 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
(ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ) ፤ (2 737 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$)
**ዐሩሲ ፡ (ዐርሲ)** ፤ 224 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
**ሸዋ** ፤ 206 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
(መናገሻ ፡ አውራጃን ፡ ጨምሮ ፥ 280 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$)
**ጐዣም** ፤ 206 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
**ጋሞ ፡ ጎፋ** ፤ 160 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
**ወሎ** ፤ 153 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
**ስሜን ፡ እና ፡ በጌምድር** ፤ 146 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
**ከፋ** ፤ 116 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
**ትግራይ** ፤ 112 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
**ኢሉባቦር** ፤ 78 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
**ሲዳሞ** ፤ 67 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
**ወለጋ** ፤ 60 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
**ባሌ** ፤ 30 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
**ሐረርጌ** ፤ 26 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
**ኤርትራ ፡** (ባሕር ፡ ምድር ፡ እና ፡ ደንከል) ፤ 18 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
**ኢትዮጵያ** ፤ 88 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$

---


[ ] ፡ ከ 1-25 ፡ ነዋሪዎች ፡ በ ፡ ኪ.ሜ $^2$ ፤
[ ] ፡ ከ 25-50 ፡ ነዋሪዎች ፡ በ ፡ ኪ.ሜ $^2$ ፤
[ ] ፡ ከ 50-100 ፡ ነዋሪዎች ፡ በ ፡ ኪ.ሜ $^2$ ፤
[ ] ፡ ከ 100-150 ፡ ነዋሪዎች ፡ በ ፡ ኪ.ሜ $^2$ ፤
[ ] ፡ ከ 150-200 ፡ ነዋሪዎች ፡ በ ፡ ኪ.ሜ $^2$ ፤
[ ] ፡ ከ 200-250 ፡ ነዋሪዎች ፡ በ ፡ ኪ.ሜ $^2$ ፤
[ ] ፡ ከ 250-300 ፡ ነዋሪዎች ፡ በ ፡ ኪ.ሜ $^2$ ፤
[ ] ፡ ከ 300-1000 ፡ ነዋሪዎች ፡ በ ፡ ኪ.ሜ $^2$ ፤
[ ] ፡ ከ 1000+ ፡ ነዋሪዎች ፡ በ ፡ ኪ.ሜ $^2$ ።

## የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ወቅት ፥ የሀገራዊ ፡ ከዋኟ ፡ ጉባኤ ፡ አባላት ፡ ምጣኔ ፥ በክፍላተ ፡ ሀገሩ ፡ ነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ መሠረት ።

(የነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ ግምት ፡ ለ 2015 ፡ ዓ.ም. ፥ በ 1962 ፡ ዓ.ም.ቱ ፡ የጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ አከፋፈል ፡ መሠረት ። )

| ክፍለ ፡ ሀገር | ቢጋር | የነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ (በሚልዮን) ለ 2015 ፡ ዓ.ም. | የተወካዮች ፡ ብዛት ፡ (በ 1 ፡ ተወካይ ፡ ለ 200'000 ፡ ነዋሪዎች ፡ ሒሳብ) |
|---|---|---|---|
| መናገሻ ፡ አውራጃ (ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ) |  | 8.5 ፡ ሚልዮን ፡ ነዋሪዎች (6.3[11] ፡ ሚ.) | 43 ፡ ተወካዮች (32 ፡ ተወካዮች) |
| ሸዋ |  | 16.7 ፡ ሚልዮን ፡ ነዋሪዎች (25.2 ፡ ሚልዮን ፥ የመናገሻ ፡ አውራጃን ፡ 8.5 ፡ ሚልዮን ፡ ነዋሪዎች ፡ ጨምሮ) | 84 ፡ ተወካዮች |
| ጐጃም |  | 13.4 ፡ ሚልዮን ፡ ነዋሪዎች | 67 ፡ ተወካዮች |
| ወሎ |  | 12.8 ፡ ሚልዮን ፡ ነዋሪዎች | 64 ፡ ተወካዮች |
| ስሜን ፡ እና ፡ በጌምድር |  | 12.2 ፡ ሚልዮን ፡ ነዋሪዎች | 61 ፡ ተወካዮች |
| ሲዳሞ |  | 8.3 ፡ ሚልዮን ፡ ነዋሪዎች | 42 ፡ ተወካዮች |
| ትግራይ |  | 7.8 ፡ ሚልዮን ፡ ነዋሪዎች | 39 ፡ ተወካዮች |
| ሐረርጌ |  | 7.2 ፡ ሚልዮን ፡ ነዋሪዎች | 36 ፡ ተወካዮች |

11 የዐዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ የነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ ባማካይ ፡ በዓመት ፡ 2.8% ፡ እያደገ ፥ በ 64 ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ በ 1948 ፡ ዓ.ም. ፡ ከነበረበት ፡ 1 ፡ ሚልዮን ፥ በ 2015 ፡ ዓ.ም. ፡ 6.3 ፡ ሚልዮን ፡ ደርሷል ፡ ተብሎ ፡ ይገመታል ። ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ የሚገኝበት ፡ የመናገሻ ፡ አውራጃ ፡ ነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ እድገት ፡ ግን ፡ በዚያው ፡ በ 1.18% ፡ አማካይ ፡ ሀገራዊ ፡ ዓመታዊ ፡ የነዋሪዎች ፡ እድገት ፡ መጠን ፡ ተሰልቷል ።

| ክፍለ ፡ ሀገር | ቢጋር | የነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ (በሚልዮን) ከ 2015 ፡ ዓ.ም. | የተወካዮች ፡ ብዛት ፡ (በ 1 ፡ ተወካይ ፡ ከ 200'000 ፡ ነዋሪዎች ፡ ሒሳብ) |
|---|---|---|---|
| ጋሞ ፡ ጎፋ |  | 6.7 ፡ ሚልዮን ፡ ነዋሪዎች | 34 ፡ ተወካዮች |
| ከፋ |  | 6.7 ፡ ሚልዮን ፡ ነዋሪዎች | 34 ፡ ተወካዮች |
| ዐሩሲ ፡ (ዐርሲ) |  | 5.6 ፡ ሚልዮን ፡ ነዋሪዎች | 28 ፡ ተወካዮች |
| ወለጋ |  | 4.5 ፡ ሚልዮን ፡ ነዋሪዎች | 23 ፡ ተወካዮች |
| ኢሉባቦር |  | 3.9 ፡ ሚልዮን ፡ ነዋሪዎች | 20 ፡ ተወካዮች |
| ባሌ |  | 3.9 ፡ ሚልዮን ፡ ነዋሪዎች | 20 ፡ ተወካዮች |
| ኤርትራ (ባሕር ፡ ምድር ፡ እና ፡ ደንከል) |  | 3.2 [12] ፡ ሚልዮን ፡ ነዋሪዎች | 16 ፡ ተወካዮች |
| ኢትዮጵያ |  | 121.4 ፡ ሚልዮን [13] ፡ ነዋሪዎች | በድምሩ ፡ 611 ፡ ተወካዮች ። |

12 የክፍለ ፡ ሀገር ፡ ኤርትራ ፡ ነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ በ 1938 ፡ ዓ.ም. ፡ ከነበረበት ፡ 1 ፡ ሚልዮን ፡ በ 2015 ፡ ዓ.ም. ፡ 4 ፡ ሚልዮን ፡ መድረስ ፡ ነበረበት ። ነገር ፡ ግን ፥ ባለፉት ፡ 50 ፡ ዓመታት ፡ በክፍለ ፡ ሀገሩ ፡ የደረሰው ፡ የርስ ፡ በርስ ፡ ጦርነት ፡ ባስከተለው ፡ ነውጥ ፥ ካ 1 ፡ ሚልዮን ፡ ያላነሱ ፡ ነዋሪዎች ፡ ወደስደት ፡ ዓለም ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሌሎች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክፍሎች ፡ በመፍለሳቸው ፡ ምክንያት ፥ በ 2015 ፡ ዓ.ም. ፥ የክፍለ ፡ ሀገሩ ፡ የነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ ከ 3.2 ፡ ሚልዮን ፡ እንደማይበልጥ ፡ ይገመታል ።

13 እውጭ ፡ ሀገር ፡ የሚኖሩ ፡ 3.3 ፡ ሚልዮን ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ ሳይጨምር ፥ በ 2015 ፡ ዓ.ም. ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩ ፡ ነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ (1.1 ፡ ሚልዮን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጎችን ፡ ጨምሮ) ፡ 122.5 ፡ ሚልዮን ፡ ይገመታል ።